ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ
የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

“የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና የረቡኒ እና ሰላም ነው?
ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና”

በ

ምኞት ወርቁ

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ

ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ
የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

“የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና የረቡኒ እና ሰላም ነው?
ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና”

በ

ምኞት ወርቁ

የጥናቱ አማካሪ

መምህር ምንያህል ተሾመ

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገላት መሆኑን አረጋግጣለው።

የአማካሪው ስም _____

ፊርማ _____

ይህ በተማሪ ምኞት ወርቁ "የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና "የረቡኒ እና ሰላም ነው?" ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና" በሚል ርዕስ የተሰራው የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥናት ደረጃ ያሟላ እና የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው። ይህም በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል።

ፈታኝ 1 _____

ፊርማ _____

ፈታኝ 2 _____

ፊርማ _____

ነሐሴ 2013 ዓ.ም

ምስጋና

በዚህ ምድር ላይ ለተፈጠሩ የህይወቴ ፈተናዎች እና ደስታዎች ሁሉ ምክኒያቱ አንተ ነህና የድንግል ማሪያም ልጅ አማኑኤል ተመስገን! ዘኒዬ እናቴ ያንቺ ፀሎት እና አባ ያንተ የፍቅር ቁጣ እዚህ እንደደርስ አድርጎኛልና እድሜ እና ጤና ይስጥልኝ! አጎቴ(ጋሺዬ) ፣ ዘመዶቼ እና ወዳጆቼ በሙሉ ላደረጋቹልኝ ነገር ሁሉ እግዚአብሄር ያክብርልኝ። ሲከፋኝም ስደሰትም ስሜቴን ለምትጋራኝ ዉዱ ጓደኛዬ ኪያ አመሰግኛለሁ። በቴአትር ትምህርት ክፍል ዉስጥ በልዩነት ከጎኔ ለነበራችሁ መምህራን እግዚአብሄር ከጎናቹ ይሁን። ይህን ጥናት አቅሜን ሁሉ ተጠቅሜ እንድሰራ እንደ መምህር ሳይሆን እንደ ወንድም ለረዳኝ መምህር ምንያህል ተሾመ ምስጋናዬ ከልብ ነው። ሃሳብ በመስጠት በልዩነት ከጎኔ ለነበሩ ጓደኞቼ ምስጋናዬ ይድረስ ። በመጨረሻም ስለ ቅድስት ይልማ እንዲሁም ያነሳኋቸው ሃሳቦች ላይ ሁሉ መረጃ በመስጠት ለረዱኝ ሁሉ አመሰግናለው።

አበርክቶ

ከእግዚአብሄር ቀጥሎ ሀገራችንን ጠባቂ ለሆኗት ለኢትዮጲያ መከላከያ ሰራዊት እንዲሁም ለጥናታዊ ፅሁፌ በአስደናቂ ስራዎቿ መነሻ ለሆነቺኝ ደራሲ እና አዘጋጅ ቅድስት ይልማ ይሁንልኝ።

መታሰቢያነቱ

ሁሌም ለምትናፍቀኝ የምርቃቴን ቀን ስንጠብቅ ድንገት ሳላስበው ለተለየኸኝ ውድ ወንድሜ አቤል ወርቁ ይሁንልኝ።ነብስህን በአፀደ ገነት ያኑረው።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና የረቡኒ እና የሰላም ነው? ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። ጥናቱ የሚያተኩረው የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ ፣ ረቡኒ ፊልም ከቅድስት ይልማ የህይወት ተሞክሮ ጋር ያለው ዝምድና ፣ ረቡኒ ፊልምን ከፊልም ትወና ማለትም ትወና ከአካላዊ ፣ ከድምፅ ፣ ከስሜት አንፃር መተንተን እንዲሁም ሰላም ነው? ፊልምን ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር ይዘታዊ ትንተና መስጠት ላይ ነው። ይህንንም በቃለ መጠይቅ ፣ መፅሃፍቶች በማገላበጥ ፣ እንዲሁም ከዚ በፊት የነበሩ የቅድስት ይልማ ቃለ መጠይቆች በማየት ጥናቱ በዚህ መልኩ ቀርቧል። የጥናቱ አላማ የቅድስት ይልማን የህይወት ታሪክ እና ለረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና መስጠት ነው።

ማውጫ

ርዕስ **ገጽ**

ምስጋና I

አበርክቶ II

መታሰቢያነቱ III

አጠቃሎ IV

ምዕራፍ አንድ 1

1. መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 2

1.2. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 3

1.3 የጥናቱ አላማ 3

1.3.1. የጥናቱ አብይ ዓላማ 3

1.4. የጥናቱ ንዑስ አላማ 3

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ 4

1.6. የጥናቱ መጠነ ርዕይ 4

1.7. የጥናቱ ዘዴ 4

1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች 5

1.9. የጥናቱ አወቃቀር 5

ምዕራፍ ሁለት 6

2. ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት 6

2.1. ክለሳ ድርሳናት 6

2.1.1. የህይወት ታሪክ ምንነት 6

2.1.2 የፊልም ምንነት 6

2.1.3. የፊልም ባህሪያት 7

2.1.4. የፊልም ዝግጅት ምንነት 8

2.1.5. የፊልም ዝግጅት አላባውያን 8

2.1.6. የእንስታዊነት ምንነት 10
2.1.7. የእንስታዊነት አይነቶች 10
2.1.8. የይዘታዊ ትንተና ምንነት 12
2.1.9. የተዛማጅ ዕሁፎች ቅኝት 13
ምዕራፍ ሶስት 14
3. የመረጃ ትንተና 14
3.1. የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ 14
3.2 የረቡኒ ፊልም ታሪክ 15
3.2.1. የረቡኒ ፊልም ርዕሰ ጉዳይ እና የቅድስት ይልማ የህይወት ተሞክሮ 16
3.2.2. የረቡኒ ፊልም ትወና 17
3.2.1. የረቡኒ ፊልም ግብዐተ ድምፅ አጠቃቀም 20
3.3. የሰላም ነው ፊልም ታሪክ 21
3.3.1. ሰላም ነው? ፊልም ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር 22
ምዕራፍ አራት 23
4.1. ማጠቃለያ 23
ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው _____ 30
ዋቢ መጽሃፍት

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

የሰዎችን የህይወት ታሪክ ፅፎ ማስቀመጥ አሁን የተጀመረ ተግባር አይደለም። የህይወት ታሪክ በራሱ በግለሰቡ እንዲሁም በሌሎች ሰዎች ተፅፎ መቀመጡ የተለመደ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ በህይወት እና በስራ ልምዳቸው የካበቱ ግለሰቦችን የስራ እና የህይወት ተሞክሮአቸውን ማጥናት የተሻለ አርቆ አሳቢ ትውልድ ለመፍጠር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ይህ ጥናት በሃገራችን ኢትዮጵያ በኪነ-ጥበብ ኢንዱስትሪ ውስጥ በተለይም በፊልሙ ዘርፍ ላይ ጉልህ ሚና ካላቸው እንስቶች መካከል አንዷ ሰለሆነችው ደራሲ ፣ አዘጋጅ እና ፕሮዲዩሰር ቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና ከፊልም ሰራዎቿ መካከል ለረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና መስጠት ላይ ያተኩራል።ቅድስት ይልማ ከ1990ዎቹ ጀምሮ በድርሰት ፣ በዝግጅት እና በፕሮዲዩሰርነት ከ5 በላይ የሚሆኑ ፊልሞችን ሰርታለች። ከእነዚህም ፊልሞች መካከል ረቡኒ፣ ታዛ ፣ ጢባጢቤ ፣ መባ እና ሰላም ነው? ተጠቃሽ ናቸው። የቅድስት ይልማን ፊልሞች በሃገራችን ውስጥ ከሚሰሩ ፊልሞች በተለየ ሃገራዊ እይታ በሃገራችን ብዙ የማናውቃቸውን ታሪክ ጠቀስ እና ባህላዊ ይዘት ያላቸውን እንዲሁም አዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮችን እያነሳች የምትሰራ በተለይም ሴት ልጅ በሃገራችን ከሚሰጣት የችሎታ መጠን አስተሳሰብን በመለወጥ ታሪኳን እና ባህሏን በሙያዋ አማካኝነት ለህብረተሰቡ በማድረሷ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የዚህችን እንስት የህይወት ታሪክ እና ረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞችን በማንሳት ይዘታዊ ትንተና መስጠት ላይ ያተኩራል። የቅድስት “ረቡኒ” የተሰኘው ፊልም ላይ የተለያዩ ባህላዊ መድሃኒቶች ከሃገራችን ተወስደው ለእኛው በከፍተኛ ዋጋ እንደሚሸጡ እና ለባህላዊ እሴቶቻችን ዋጋ እንዳልሰጠን ያሳያል። ይህ ሃሳብ “ሞሪንጋ” የተባለ መድሃኒት በእኛ ሃገር “ሽፈራው” የሚል ሰያሜ ያለው ለተለያዩ በሽታዎች የሚጠቅም የቅጠል አይነትን ጥቅም ነው ሚያነሳው። አጥኚዋም ሽፈራው የተባለውን ቅጠል በአካባቢዋ ለደም ግፊት ሲጠቀሙበት ስላየች የበለጠ ሰለ መድሃኒቱ እውቀት እንዲኖራት ሰላደረጋት እና ሰለዚህ ቅጠል እና በሃገራችን ሰላሉ የተለያዩ መድሃኒቶች ተጨማሪ ምልከታዎችን እንድታደርግ እና ሰለ ረቡኒ ፊልም በጥልቀት እንድታስብ አድርጓታል። እንዲሁም “ሰላም ነው?” ፊልም አዲስ ይዘት ያለው ፊልም ሲሆን ሴት ልጅ ለምተወዳቸው ሰዎች ስትል እራሷን እንደ ወንድ ሰይማ መስዕዋትነት ስትከፍል የሚያሳይ ፊልም ነው። አጥኚዋም በዚህ ፊልም ትኩረቷን የሳበው እዚህ ፊልም ላይ ያለው የሴት ገፀ ባህሪ አሳሳል በአካባቢዋ ከምታውቃቸው ሴቶች በተለየ መልኩ በመሆኑ ማለትም ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ከሚሰጣት ስያሜ ወጥታ የፈለገችውን መሆን ትችላለች የሚለውን ሃሳብም ሰላስገነዘባት እነዚህን የቅድስት ይልማ ሁለት ፊልሞች ርዕሰ ጉዳይ ከዚህ ቀደም ባልተጠኑበት አግባብ በመፈተሽ ጥናታዊ ፅሁፍ እንድትሰራ አነሳስቷታል። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አንድን ሰው ፣ ቡድን ፣ ማህበረሰብ . . . የመሳሰሉትን ነጥሎ በመውሰድ ከተለያዩ መስፈርቶች አንፃር ማጥናት /'ንጥል ጥናት'/ የሚለውን የምርምር ንድፍ ተጠቅሞ በቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና በረቡኒ እና በሰላም ነው? ፊልሞቿ ላይ ይዘታዊ ትንተና ይሰጣል። እንዲሁም የህይወት ታሪኳ ለፊልም ሰራዎቿ ታሪክ

መነሻ ናቸው? የፊልሞቿ ይዘት እና የአሰራር ጥበብ ሁለንተናዊ ፋይዳ ምንድነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በእነዚህ አራት ምዕራፎች አንስቶ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ በመጠቀም ምላሽ ይሰጣል።

1.1. የጥናቱ ዳራ

አጥኚዋ “የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና የፊልም ሰራዎቿ ይዘታዊ ትንተና” በሚል ርዕስ ለመስራት ያነሳሳት በሃገራችን የኪነ ጥበብ ዘርፍ በተለይም በፊልሙ ላይ ከተለመዱት የፊልም ይዘቶች በተለየ መልኩ በሃገራችን ስላሉና ሰለማናውቃቸው ታሪካዊ እና ባህላዊ ክንውኖችን ለማሳወቅ የምትሰራ ደራሲ ፣ አዘጋጅ እና ፕሮዲዩሰር በመሆኗ ከኪነ ጥበብ ስራዎቿ እና የህይወት ልምዷ ማህበረሰቡ እና የፊልም ባለሙያዎች ተሞክሮ እንዲወስዱ በማሰብ ነው።

1.2. ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

1. ቅድስት ይልማ ማን ናት?
2. የቅድስት ይልማ የኪነ ጥበብ ስራዎች ምን ምንድናቸው?
3. የቅድስት ይልማ ፊልሞች ከርዕሰ ጉዳይ አንፃር በብዛት ምን ላይ ያተኩራሉ? ለምን?
4. “ረቡኒ” ፊልም ከትወና እና ከግብዐተ ድምፅ አንፃር ምን ይመስላል?
5. የ“ረቡኒ” ፊልም ርዕሰ ጉዳይ ከደራሲ እና አዘጋጇ የህይወት ታሪክ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው?
6. በ”ሰላም ነው?” ፊልም ላይ ሴትነት እንዴት ተገልፁአል?

1.3 የጥናቱ አላማ

1.3.1. የጥናቱ አብይ ዓላማ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ዋና አላማ አድርጎ የተነሳው በኢትዮጲያ ፊልም ኢንዱስትሪ ውስጥ ካሉ እንስት ደራሲያን መካከል አንዷ ሰለሆነችው ደራሲ፣አዘጋጅ እና ፕሮዲዩሰር ቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እንዲሁም ረቡኒ እና ሰላምነው? የተሰኙ ፊልሞቿን ከእንስታዊነት፣ከትወና እና ከግብአተ ድምፅ አንፃር ትንተና መስጠት ላይ ነው።

1.4. የጥናቱ ንዑስ አላማ

- የቅድስት ይልማን የህይወት ታሪክ እና የረቡኒ ፊልም ርእሰ ጉዳይ ያላቸውን ዝምድና መግለፅ።
- በ”ረቡኒ” ፊልም ላይ የፊልም ትወናን ከአካላዊ ፣ ከድምፅ ፣ ከስሜት አንፃር መተንተን።
- የረቡኒ ፊልም ግብዐተ ድምፅ በተፈጥሮአዊ ድምፅ እና በሙዚቃ የተገለፀበትን ዘዴ እና አጠቃቀማቸውን መተንተን።
- “ሰላም ነው?” የተሰኘው ፊልም ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር ማለትም ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ከተሰጣት የፆታ መደብ አኳያ ንፅፅራዊ ዳሰሳ ማድረግ።
- ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ነው።

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ከቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እንዲሁም በፊልሞቿ አማካኝነት የምታስተላልፋቸውን ጠቃሚ የሆኑ መልዕክቶች ሰዎች የፊልሞቿን ፅንሰ ሃሳብ በመረዳት በስራዎቿ እንዲሁም ከሷ የግል የህይወት ታሪክ እና አስተሳሰቧ ልምድና ትምህርት እንዲያገኙ ያደርጋል። በፊልም ኢንዱስትሪ ላይ ላሉ ባለሙያዎች ሚያስተላልፉት ጠንካራ መልዕክት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በተጨማሪም በዚህ አይነት እና መሰል ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናታቸውን ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እንደ መነሻ እንዲሁም እንደ ተዛማጅ ፅሁፍ ሆኖ ያገለግላል።

1.6. የጥናቱ መጠነ ርዕይ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የቅድስት ይልማን የህይወት ታሪክ እንዲሁም ከፊልም ስራዎቿ መካከል “ረቡኒ” እና “ሰላም ነው?” ለሚሉት ፊልሞች ከግብዐተ ድምፅ ፣ ከፊልም ትወና እና ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር ይዘታዊ ትንተና መስጠት ላይ የተወሰነ ነው። ምክኒያቱም ”ረቡኒ” ፊልም የሚታወቁ ግን ቦታ ያልተሰጣቸው ባህላዊ ክንውኖች በማሳወቁ እና አዘጋጇ ያላትን ሃሳብ በደንብ ያንፀባረቀችበት በመሆኑ ነው። እንዲሁም“ሰላም ነው?” የሚለው ፊልም ደግሞ ሴት ልጅን በማህበረሰቡ ከሚሰጣት እይታ በተለየ መንገድ በመሳሉ ነው።

1.7. የጥናቱ ዘዴ

አጥኚዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት የተጠቀመችው የአጠናን አይነት ያለው እንዳወቀ ሙሉ “የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር “ በሚለው መፅሃፉ ላይ ያሰፈረውን “ንጥል ጥናት” የሚለውን የምርምር ንድፍ ሲሆን ይህም አንድን ሰው ፣ ቡድን ፣ ማህበረሰብ ወይም ተቋም ከሌሎች ነጥሎ በመውሰድ በጥልቀት ከተለያዩ መስፈርቶች አንፃር ለማጥናት የሚያስችል የምርምር ንድፍ አይነት ነው። አጥኚዋም ይህን የምርምር ንድፍ የተጠቀመችው የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና ከፊልሞቿ መካከል በረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጋ ስለምትሰራ ነው።

1.7.1. የጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

አጥኚዋ ስለ ቅድስት ይልማ የጠራ እና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ቅድስት ይልማን ስለስራዎቿ ያላትን አመለካከት ፣ የቅርብ ወዳጆቿን ስለ ባህሪዋ ፣ ጓደኞቿን ስለ አመለካከቷ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ፣ ከዚ በፊት የነበሯትን የቴሌቪዥን ቃለ ምልልስ እንደማጣቀሻ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስባለች።

1.7.1.1 ቃለ መጠይቅ

አጥኚዋ ይሄንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማድረግ ከተጠቀመቻቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ቃለመጠይቅ ስለሆነ የመጀመሪያው ቅድስት ይልማ በአርትስ ቲቪ ላይ ደረጄ ሃይሌ ስለአዲሱ ተከታታይ ድራማዋ ያደረገላት ቃለ መጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አጥኚዋ ለቅድስት ይልማ በስልክ አማካኝነት ለበፊት ስራዎቿ እንዲሁም

ስለወደፊት ሃሳቧ ያደረገችው ቃለ መጠይቅ ነው። ሶስተኛው እና የመጨረሻው ደግሞ ለወዳጆቿ እና ጓደኞቿ ያደረገችው ስለ ቅድስት ይልማ ባህሪይ ያደረገችው ቃለ መጠይቅ ነው።

1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች

አጥኚዋ ይህን ጥናት ስታደርግ ካጋጠሟት ችግሮች መካከል ዋነኛው አጥኚዋ ቅድስት ይልማን ቃለመጠይቅ በምታደርግበት ሰአት ሰለግል ህይወቷ መናገር ባለመፈለጓ ጥናቱ ችግር ቢያጋጥመውም እንዲሁም በአንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ዉስጥ 3 ርዕሰ ጉዳዮችን አንስታ በመስራቷ መረጃዎችን የመስብሰቢያ ጊዜ እጥረት ቢያጋጥማትም ይህንንም ያጋጠማትን ችግር ሰለ ቅድስት ይልማ ከተለያዩ ከሚያውቋት ጓደኞቿ እንዲሁም ቤተሰቦቿ ያገኘቻቸውን መረጃዎች አቀናጅታ በመጠቀም እንዲሁም የሶስቱን ርዕሶች ዋና ዋና ሃሳቦቹን ብቻ በማንሳት ችግሮቹን በመፍታት ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለመስራት ችላለች።

1.9. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው። በየምዕራፉ ውስጥ የሚካተቱ ነጥቦች እንደሚከተሉት ቀርበዋል። ምዕራፍ አንድ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ የጥናቱ አላማ /አብይ እና ንዑስ/ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ መጠነ ርዕይ ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም የጥናቱ አወቃቀር የሚሉትን ያካትታል። ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት የሚሉትን የያዘ ሲሆን በክለሳ ድርሳናት ስር የህይወትታሪክ ምንነት ፣ የፊልም ምንነት ፣ የፊልም ዝግጅት ምንነት፣ የፊልም ባህሪያት ፣ የፊልም አሰራር ደረጃዎች ፣ የእንስታዊነት ምንነት ፣ የእንስታዊነት አይነቶች የሚለውን ይዟል። ምዕራፍ ሶስት የቅድስት ይልማን የህይወት ታሪክ ፣ የ “ረቡኒ”ፊልም ከቅድስት ይልማ ህይወት ተሞክሮ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድነው? የረቡኒ ፊልም ትወና ከስውነት ፣ ከድምፅ ፣ ክስሜት አንፃር እና ግብዐተ ድምፅ ከተፈጥሮ እና ከሙዚቃ መሳሪያዎች አጠቃቀም አንፃር ምን ይመስላል? እንዲሁም “ሰላምነው”? የተሰኘውን ፊልም ከጀንደር እንስታዊነት ማለትም ማህበረሰባዊ የፆታ ውክልና አንፃር ሴትነት እንደት ተገልፁአል ለሚሉት ነጥቦች ይዘታዊ ትንተና መስጠት የሚሉትን ይዟል። ምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ የያዘ ሲሆን በመጨረሻም ቃለ መጠይቅ እና አባሪ ተካትቷል።

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

2.1. ክለሳ ድርሳናት

2.1.1. የህይወት ታሪክ ምንነት

የህይወት ታሪክ ማለት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ሰለ አንድ ሰው ብቻ የሚተረክበት የህይወት ተሞክሮ ማስታወሻ ነው። የህይወት ታሪክ አንድ ሰው ከውልደቱ ጀምሮ የህይወት ታሪኩ በፅሁፍ እስከቀረበበት ጊዜ ያለውን የህይወት ተሞክሮ በፅሁፍ ተሰንዶ የምናገኝበት ትምህርታዊ ማስረጃ ነው። ብርጊቱ ፖሲንግ "አንደርስታንዲንግ ባዮግራፊ" በሚለው መፅሃፏ ላይ "የህይወት ታሪክ ማለት ታሪክ ከሚነገርባቸው ዘውጎች መሃል አንዱ ነው። ይህም በትረካዊ እና በትንታኔያዊ መንገድ ይቀርባል።"[1] (7 ፣ 2017) ይህም ማለት የህይወት ታሪክ በሁለት መንገዶች ሊፃፍ ይችላል እነሱም በትረካ ማለትም የግለሰቡ ታሪክ በሌላ ሰው ሲፃፍ እንዲሁም በትንታኔያዊ ሲባል ደግሞ ግለሰቡ ራሱ ተንትኖ ሚፅፍበት ዘዴ ማለት ነው። የታሪክ ምሁራኖች የህይወት ታሪክ መፃፍ የተጀመረው ስነ ፅሁፍ እንደተጀመረ ነው ይላሉ። ከጥንት ዘመን አንስቶ እስከ አሁኑ ዘመን ድረስ ባሉት ጊዜያት ብዙ ነገሮች እየተለወጡ እና እየተሻሻሉ መጥተዋል። አብዛኞቹ ምሁራኖች በዚያን ዘመን የጀግኖችን የህይወት ታሪክ በመፃፍ እንደተጀመረ ይገልፃሉ።የታሪክ ምሁራኖችም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ። ኒግሌ ሃሚልተን እና ሃንስ ሬንደርስ "ዘ ኤቢሲ ኦፍ ሞደርን ባዮግራፊ" በሚለው መፅሃፋቸው ላይ "የህይወት ታሪክ በርግጥም የግል ጥናት ነው። ቃሉ እንደሚገልፀው በተለያየ መንገድ የሰዎችን ያለፈ እና የአሁን የግል የህይወት ታሪክ አጠቃሎ ማስቀመጥ ወይም መፃፍ ነው።"[2] (16 ፣ 2018) ይህ ማለት የሰው ልጅ ከውልደቱ ጀምሮ በአስተዳደጉ ውስጥ ያለው ሂደት ፣ የቤተሰብ ሁኔታ የትምህርት እንዲሁም የስራ ደረጃን የህይወት ታሪኩ እስኪፃፍ ድረስ ያለው የኑሮ ሂደት የሚተረክበት አንድ የፅሁፈ ታሪክ ዘውግ ነው።

2.1.2 የፊልም ምንነት

ፊልም ማለት ቀጥተኛ የአማርኛ ትርጉሙ "ተንቀሳቃሽ ስዕል" ማለት ሲሆን በአንድ ሰው አዕምሮ ውስጥ የነበረን ሃሳብ ወደ ሚታይ ምስል በመቀየር ሃሳቡን በተንቀሳቃሽ ድርጊት አማካኝነት ወደ ተመልካች የሚደርስበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው። በመሆኑም ፊልም በደራሲው ምናብ ውስጥ ያለውን አስተማሪም ሆነ አስቂኝ ታሪክ በአዘጋጁ አማካኝነት ወደ ተንቀሳቃሽ ምስል ተቀይሮ ለህብረተሰቡ የሚቀርብበት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው። ዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ" በሚለው መፅሃፉ ላይ ፊልምን እንደዚህ ሲል ያብራራዋል። "የፊልም ጥበብ በተንቀሳቃሽ ምስል አማካኝነት ለተደራሲያን ታሪክ የሚነገርበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት የሰው ልጆች ኪነ ጥበባዊ የተግባቦት መንገድ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ታሪኩ የሚነገረው በድርጊት እና በምስል ስለሆነ የፊልም ጥበብ እይታዊ ጥበብ ነው ማለት እንችላለን።" (2010 ፣ 18)

ፊልም የሰው ልጅን የእለት ተዕለት ኑሮ የሚተርክ በመሆኑ ተመልካቹ ውስጡ ያለውን ችግር ፣ ማግኘት ፣ ደስታ እና ሃዘኑን ሚወጣበት እና ሚያጣጥምበት መንገድ ይማርበታል ማለት ነው። ፊልም ለሁሉም ሰው ተደራሽ የመሆን አቅም አለው። ምክኒያቱም ፊልሙ የተሰራበትን ቋንቋ የማይችል ተመልካች ከሆነ በማየት ብቻ የፊልሙን ሃሳብ ሊረዳ ይችላል።

ፊልም በገሃዱ አለም የሚታየውን እውነታ ለተመልካቹ ግልፅ በሆነ መልኩ በተንቀሳቃስሽ ምስል የሚገለፅበት መንገድ ነው። ብዙውን ጊዜ ፊልም ከንግግር ይልቅ በምስል ሃሳቡን ይገልፃል። ይህም ማለት ለምሳሌ በፊልሙ ውስጥ ያለ አንድ ተዋናይ ገፀ ባህሪው ሚደነግጥ ከሆነ ከንግግር ይልቅ በፊቱ ፣ በእጁ እና በሰውነቱ ላይ ያለውን የድንጋጤ ስሜት በመቅረፀ ምስሉ አማካኝነት ወስዶ ያሳያል ማለት ነው።

በተጨማሪም በምስሉ የሰው ልጅ የእለተለት ኑሮ ሃዘን ፣ ደስታ ፣ ቁጭት ፣ ትዝታ ፣ ፍቅር ... የመሳሰሉትን ስሜቶች የሚንፀባርቁበት ሰለሆነ ሰዎች ወደራሳቸው ስሜት በማጋባት ሃዘናቸውን በደስታ ፣ ጥላቻን በፍቅር እንዴት እንደሚወጡ የሚያሳይ ጥበባዊ መንገድ ነው። አዲስ ተስፋዬ “የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ብልሃት” በሚለው መፅሃፉ ላይ ይህንን ሃሳብ እንዲህ ያጠናክረዋል። “ፊልም ታሪክን በምስል ፣ በድርጊት ፣ እና በእንቅስቃሴ ቅንብር የመንገር ጥበብ ነው። ፊልም ታሪኩን የሚሸከሙ ባለታሪኮችን የጊዜና የቦታ ገደብ ሳይኖራቸው ፣ የሚኖሩትን፣ የሚያጋጥማቸውን ችግር የሚወጡባቸውን ስልቶች ለተመልካች ለማጋራት ብቻ ሳይሆን በማሳየት ታሪክን የመንገር መንገድ ነው።” (2005 ፣ 34) ከዚህ በመነሳት ፊልም ማለት የዕለት ተዕለት ኑሮአችንን በጥበባዊ ድርጊት ፣ ስሜት እና ድምፀት አማካኝነት ለተመልካች የሚደርስበት የኪነጥበብ ዘርፍ ነው። ፊልም ማለት ተመልካቾች ችግሮችን እንዲሁም የተለያዩ ስሜቶችን እንዴት መወጣት እንደሚችሉ ትምህርት የሚወስዱበት እይታዊ የጥበብ ዘርፍ ነው።

2.1.3. የፊልም ባህሪያት

ፊልም የተለያዩ ባህሪያት ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል የመጀመሪያው በተንቀሳቃሽ ምስል እና ድምፅ መቅረቡ እንዲሁም በተጨማሪም ከሌሎቹ የኪነ ጥበብ ዘርፎች ይልቅ በሰው ልብ ውስጥ ዘልቆ የሚገባ የጥበብ ዘርፍ ነው። ይህም የሚሆነው የተለያዩ ጊዜና ቦታዎችን ተመልካቹ ሃሳቡ ሳይበታተን በአጭር ሰአት ዉስጥ በማቅረቡ ነው። ለምሳሌ ፊልሙ የተቀረፀው አሁን ባለንበት ዘመን ላይ ቢሆን ከ100 አመታት በፊት የነበሩ ታሪኮችን አሁን ካለንበት ዘመን ታሪክ ጋር አዋህዶ በ 1 ወይም በ 2 ሰአታት ዉስጥ እጥር ምጥን አደርጎ ያቀርባል። ወሰንየለህ ጥላሁን “የፊልም ጥበብ ቅኝት” በሚለው መፅሃፉ እንዲህ ሲል አጠናክሮታል። “ፍሰት ያለው ትዕይንት ፣ ድምፅ እና እንቅስቃሴ የአሁንነትና የእዚያውነት ደስታን ስለሚፈጥር ተመልካቹን በሲኒማው ሂደት ውስጥ በተመስጦ ይጨምረዋል። ስለዚህ በፊልም አማካኝነት የሚፈጠረው ሰመመን የእውናዊውን አለም ቅርፅና ስሜት መምሰል ይችላል።” (2005 ፣ 4)

የፊልም ጥበብ በአንድ ቀረፃ ብቻ ሙሉ ምስል የሚታይበት ሳይሆን አንድ ፊልም የሚሰራው የተለያዩ እና የተቆራረጡ ምስሎችን በመቀጣጠል እና ወደ አንድ አምጥቶ በማቀነባበር ነው። ጳውሎስ አእምሮ “የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ” በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዲህ ገልፆታል። “ተንቀሳቃሽ ምስል በብዙ ምስሎች አማካኝነት የሚሰራ

እና አንድ ሁነኛ ታሪክ የሚተረክበት የጥበብ ስራ ነው።" (167 ፣ 2010) ፊልም የተለያዩ የቀረፃ ቦታና ጊዜ ተጠቅሞ በአንድ ጊዜ እና ቦታ እንደተሰራ አድርጎ የሚያሳምን የጥበብ ዘርፍ ነው።

2.1.4. የፊልም ዝግጅት ምንነት

የፊልም ዝግጅት ማለት ከፊልም ፅሁፍ መተርጎም ጀምሮ ፊልም ሆኖ ለተመልካች እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂደት ነው። እነዚህም ሂደቶች የፊልም ፅሁፍ መተርጎም ፣ ተዋናይ መምረጥ ፣ ቀረፃው የሚካሄድበትን ቦታ መምረጥ ፣ ካሜራ ፣ ግብዐተ ድምፅ ፣ ግብዐተ ብርሃን ፣ አልባሳት ፣ የገፅቅብ እንዲሁ ቅንብር የመሳሰሉት ናቸው። በእነዚህ የዝግጅት ሂደቶች አማካኝነት አንድ ፊልም ብቁ ሆኖ ይወጣል። ይህንንም ጳውሎስ አእምሮ "የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ" በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዲህ ሲል አስፍሮታል "የፊልም ዝግጅት በፅሁፍ የተቀመጠን ታሪክ በምስል እና በቅንብር ሃይል የመተርጎም ጥበብ ነው።" (2010 ፣ 56) የፊልም ዝግጅት በፊልም ዉስጥ ዋናውን ሚና የሚጫወት የስራ ድርሻ ነው። ስለዚህም ለፊልሙ መሳካት እና ማማር የመጀመሪያውን ድርሻ የሚወስደው አዘጋጅ ነው። ዝግጅቱን የሚያከናው ባለሙያ በመሆኑ አዘጋጁ የፊልሙ ፈጣሪ ነው ለማለት አያስቸግርም። የፊልም ባለሙያዎችም ስለ አዘጋጆች በዙ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ ከነዚህም መካከል ይህን ሃሳብ ለማጠናከር ወሰንየለህ ጥላሁን "የፊልም ጥበብ ቅኝት" በሚለው መፅሃፉ ላይ ሰለ አዘጋጅ እንዲህ ሲል ሃሳብ ሰጥቷል። "አዘጋጆች ፊልም ሲሰሩ የሚፈፅሟት እያንዳንዷ ድርጊት የዘይቤአቸው አንድ አካል ነች። ምክኒያቱም በሆነ ብልጠት በተግባር ለመፈፀም ወይም ለመተርጎም የሚወስዷት እያንዳንዷ ውሳኔ የገፃ ራሳቸውን አመለካከት ታንፀባርቃለች እናም የገፃ ስብዕናቸውን በፊልሙ ውስጥ አድምቀው ይከትቱበታል።"(300 ፣2005) አንድ አዘጋጅ ፊልም በሚያዘጋጅበት ወቅት የተዋናይ መረጣ ፣ የአልባሳት ፣ የገፅ ቅብ ... ሁሉም በአዘጋጁ መሪነት ነው ሚካሄዱት። በዚህም ምክኒያት አዘጋጁ በራሱ አመለካከት ፣ አስተሳሰብ እና የዉስጥ ስሜት አማካኝነት ነው ፊልሙን የሚያስኬደው።

2.1.5. የፊልም ዝግጅት አላባውያን

አንድን የፊልም ፅሁፍ ወደ ጥሩ ተንቀሳቃሽ ምስል ለመቀየር የፊልም ዝግጅት ዋናው እና አስፈላጊው ነገር ነው። ዝግጅት ደግሞ ያለ አላባውያን ድጋፍ ብቻውን ሊቆም አይችልም። ምክኒያቱም አላባውያን ማለት አንድ የኪነ ጥበብ ሰራ በዉስጡ የሚይዛቸው ይዘቶች ማለት ነው። በፊልም ዝግጅት ዉስጥም የተለያዩ አላባውያን አሉ እነዚህም የምስል ቀረፃ ፣ የቀረፃ ማእዘን ፣ መብራት ፣ የሙዚቃ እና የድምፅ ግብዐት ፣ የፊልም ትወና ፣ የፊልም ትዕይንት ግንባታ ፣ የፊልም ቅንብር ናቸው። በእነዚህ ሂደቶች አማካኝነት የአንድን ፊልም ዝግጅት በተሟላ እና በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ያደርገዋል። ይህን ሃሳብ ጳውሎስ አእምሮ "የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ" በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዲህ ሲልያጠናክረዋል። "በምስል ሃይል ታሪክን ለመተረክ የፊልም ዝግጅት አላባውያንን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። አላባውያን ስንል አንድ የስነ ፅሁፍ ወይም የኪነ ጥበብ ስራ የተሰራበት ዋና ይዘታዊ ወይም ውስጣዊ ነገሮች ማለት ነው።" (2010 ፣ 56) የፊልም ዝግጅት የአላባውያን ድምር ውጤት ነው እንጂ ራሱን ችሎ የሚቆም አይደለም ይህም ማለት አንድ ፊልም ለመሰራት የምስል ቀረፃ ፣ የቀረፃ ማእዘን ፣

መብራት ፣ የሙዚቃ እና የድምፅ ግብዐት ፣ የፊልም ትወና ፣ የፊልም ትዕይንት ግንባታ ፣ የፊልም ቅንብር. . . እነዚህን አላባውያን ማሟላት አለበት።

2.1.5.1. የፊልም ትወና

ትወና ማለት አንድ ተዋናይ የተሰጠውን ገፀ ባህሪ በሰውነት እንቅስቃሴው ፣ በድምፁ እንዲሁም ፣ በስሜት የሚሰራበት መንገድ ነው። እንዲሁም ፅሁፉን በእንቅስቃሴ ወደ ድርጊት ለመቀየር የሚጠቅምበት ዘዴ ነው። አንድ ተዋናይ ለመተወን ሲያስብ በመጀመሪያ የራሱን ባህሪ በመተው የገፅ ባህሪውን ደንብ በመላበስ ተመልካቹን በስሜት እና በድርጊት ለማሳመን የሚያደርገው ሂደት ትወና ይባላል። ይህንንም ጳውሎስ አእምሮ "የፊልም አዘገጃጀት ዘዴ" በሚለው መፅሃፉ እንዲ ገልፆታል። " በፅህፈተ ፊልሙ ውስጥ በቃለ ተውኔት ፣ በገለፃ እና በትረካ የተገለፀን ሃሳብ ወደ ድምፅና ክዋኔ የመለወጥ ዘዴ ነው።" (2010 ፣ 120) ይህም ማለት አንድ በገለፃ እና በትረካ የቀረበን ሃሳብ ስሜት በሚሰጥ የድምፅ አወጣጥ እና በሚያሳምን ድርጊት መተወን ማለት ነው። ትወና በተዋናዩ ህይወት ላይ ያልተፈጠረ ነገር ቢሆን እንኳን ተዋናዩ የተሰጠውን አዲስ ባህሪ /ገፀ ባህሪይ/ ከራሱ ጋር በማዋሃድ ተመልካቹን የሚያሳምንበት ጥበብ ነው።

በትወና ጥበብ ዉስጥ ተዋናዩ ፊልሙ ተሰርቶ እስከሚያበቃ ድረስ በገፀ ባህሪ ውስጥ ራሱን ሰጥቶ ሰለሚቆይ ከገፀ ባህሪው ጋር የሚላመድበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህ ሲሆን ደግሞ ተመልካቹን በያዘው ገፀ ባህሪ አማካኝነት የማሳመን እና ስሜት ውስጥ የመክተት ችሎታ ይኖረዋል። ዘላለም ተፈሪ "የፊልም ትወና ጥበብ" በሚለው መፅሃፉ ላይ " የፊልም ትወና ጥበብ በሰው ልጆች መካከል በሚደረግ የተግባቦት ሂደት ላይ የሚመሰረት የኪነ ጥበብ ዘርፍ ነው።" (2010 ፣ 3) ትወና ማለት አንድ ተዋናይ በስሜት ፣ በድርጊት እና በድምፁ አማካኝነት ታሪክና ስሜቱን ለተመልካች ለማጋባት የሚሰራበት የፊልም ዝግጅት አላባውያን አይነት ነው።

2.1.5.2. ግብዓተ ድምፅ

ግብዓተ ድምፅ ማለት በጆሮአችን የምንሰማቸው የተለያዩ ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ ድምፆች ናቸው። ግብዓተ ድምፅ በፊልም ዉስጥ ደግሞ የፊልሙን ሃሳብ ሰርፆ ወደ ተመልካቹ እንዲገባ የሚያደርግ እንዲሁም በፊልሙ ዉስጥ ያሉ ድርጊቶች ሁሉ ህይወት እንዲዘራባቸው የሚያደርግ የዝግጅት አላባ ነው። ይህም ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ገፀ ባህሪያት መካከል የሚደረጉ ድርጊቶችህን ለማሳካት ለምሳሌ የተኩስ ፣ የእግር ኮቴ ፣ የመብረቅ ፣ የአእዋፋት ፣ ሙዚቃ... አይነት ድምፆችን በመጠቀም ሁኔታዎቹ እና ክንውኖቹ የእውነት እንዲመስሉ የሚደረግበት መንገድ ነው። ወሰንየለህ ጥላሁን ገ/የሱስ "የፊልም ጥበብ ቅኝት" በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዲህ ብሎ ያብራራዋል "በምስል ከምናገኘው የላቀ ስሜት በመፍጠር የምንከታተለውን ትዕይንት ስፋት ፣ ጥልቀትና ዕምቅነት ያበለፅጉበታል" (2005 ፣ 213) ግብዐተ ድምፅ የራሱ የሆነ ባለሙያ አለው ይህም ባለሙያ ፊልሙ ተጀምሮ እስከሚያልቅ የሚያስፈልገውን ተፈጥሮአዊም ሆነ የተቀነባብሩ ድምፆችን ያዘጋጃል ያቀርባል። "በፊልሙ ውስጥ የሚሰሙ ድምፆች በሙሉ የሚቀርፀው እና መቅረፀ ድምፁን የሚቆጣጠረው ባለሙያ የድምፅ ባለሞያ ነው።" (ዘላለም ተፈሪ 2010 ፣ 32) ትወና ያለ ተዋናይ እንደማይሰራ ሁሉ ያለግብዓተ ድምፅ ባለሙያም ግብዐተ ድምፅ ሊሰራ አይችልም። ይህም የግብዓተ ድምፅ ባለሙያ በፊልም ዉስጥ ታሪኩን

ሊያስኬድ የሚችል ማጀቢያ ሙዚቃ ፣ መሸጋገሪያ ሙዚቃ እንዲሁም ተፈጥሮአዊ ድምጾችን በተገቢው ቦታ እና ጊዜ እንዲጠቀሙ የሚያደርግ የፊልም ባለሙያ ነው።

2.1.6. የእንስታዊነት ምንነት

እንስታዊነት ማለት ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት ይኑራቸው እንዲሁም የመደብ ክፍፍል አይኑር የሚል አስተሳሰብ የያዘ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ይህም ማለት ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው በመሆኑም እኩል መስራት ፣ እኩል ማሰብ ፣ ማሸነፍ ይችላሉ የሚለውን አስተሳሰብ የያዘ ነው። ሴት እና ወንድ ፆታ ነው እንጂ ከዛ በዘለለ የስራ ዘርፋቸው ወይም ግዳጃቸውን መቀያየር እንችላለን የሚል እሳቤም ይሏል። ነገር ግን ይሄ ንቅናቄ ሴት ልጅ የበላይ ትሁን በቻ የሚል አስተሳሰብ የለውም። ይህ ንቅናቄ በሴቶች ላይ ትኩረት አድርጎ ይነሳ እንጂ በማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር እኩልነት ያምናል።

እንስታዊነት ሴት ልጅ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እኩልነት እንዳላት ማሳየት ፣ ከሴት ልጅ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሁሉ ንቅናቄ መፍጠር ፣ ሴት ልጅን ነፃ ማውጣት እና ለሴት ልጅ ነፃ የንግግር መድረክ ማዘጋጀት የመሳሰሉትም የእንስታዊነት ባህሪያት ናቸው። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ምሁራኖች የተለያዩ ብያኔዎችን አስፈረዋል። ከነዚህም መካከል ዳዊት ግርማ እንስታዊነት በኢትዮጲያ ፍልስፍና በሚለው መፅሃፉ ላይ እንደዚህ ያብራራዋል። “እንስታዊነት በሰፊ አውድ ሲበየን ፣ ስነፅሁፍ እና ሌሎች የባህል ተዋፅያዎች የሴቶችን ኢኮኖኢያዊ ፣ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ኩነቶች ውስጥ መገለል እና መረገጥን በአንክሮ ያጠናል።” (2011 ፣ 34) ይህም ማለት ይሄ አስተሳሰብ ትኩረቱን አድርጎ ሚሰራው የሴት ልጅን ዝቅ ማለት አጥብቆ በመቃወም ላይ እና ከወንድ ጋር ያላትን የእኩልነት መጠን ለመግለፅ የተነሳሳ ነው።

እንስታዊነትን የሚያራምዱ ሰዎች የሴት እና የወንዶችን የሃሳብ ፣ የጉልበት ፣ የስልጣን ፣ የመምራት እና የመሳሰሉትን እኩልነት ያምናሉ። በዚህም ምክኒያት በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለሴት የበታች ስያሜ ወይም ድርሻ እንዳይሰጣት እና እንዳይኖራት ይታገላሉ። “እንስታዊነትን የሚከተሉ ሰዎች በሴቶች እና በወንዶች መካከል መሰረታዊ የስልጣን ሽኩቻ እንዳለ ያምናሉ። ከሚያጋጫቸው መካከል ዋነኞቹ የመደብ ክፍፍል እና የዘር ጉዳዮች ናቸው።”[3] (ኬቪን ሃሪሰን እና ቶኒ ቦይድ 2018 ፣ 296) በርግጥም ይሄ ንቅናቄ ያለምንም ምክኒያት አልተጀመረም ይሄ ንቅናቄ በሴት ልጅ ላይ ያለውን ጫና አይቶ የሴት ልጅ የበታችነትን ለማጥፋት የተነሳ ነው።

2.1.7. የእንስታዊነት አይነቶች

በዚህ ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ ያሉ ምሁራኖች እንደሚናገሩት በእንስታዊነት እንቅስቃሴ ውስጥ በርካታ የእንስታዊነት አይነቶች ሲኖሩ እነዚህም በሴት ልጅ መብት ላይ ተመርኩዘው ለሚነሱ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡ ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ሊብራል እንስታዊነት ፣ ራዲካል እንስታዊነት እና ጀንደር እንስታዊነት ተጠቃሽ ናቸው።

2.1.7.1. ሊብራል እንስታዊነት

ምሁራን እንደሚናገሩት “ሊብራል እንስታዊነት” ንቅናቄ ከጀመረ ከ20 አመት በላይ አስቆጥሯል ይህም ሴቶች ከፆታ በስተቀር በአካልም /በጥንካሬ ፣ በተክለ ሰውነት/ ሆነ በአስተሳሰብ ከወንዶች እኩል እንደሆኑ እንዲሁም

በአካል አፈጣጠራቸው /አካል ጉዳተኛ/ ካልሆኑ በማንኛውም የትምህርትም ሆነ የስራ ዘርፍ መሳተፍ እንደሚችሉ የሚሰብክ አስተሳሰብ ነው። ለዚህም ማጠናከሪያ ተክሉ አስኳሉ "የአመፃ መንገድ" በሚለው መፅሃፉ ላይ እንዲህ ሲል ያብራራዋል። "ሊብራል ፌሚኒስቶች ወንዶችና ሴቶችን ለያይቶአቸዋል ያሏቸውን ህጎች ፣ ሴቶችን ለመጨቆን በማሰብ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ የወንድ እና የሴት ልዩነትን በተሻለ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሴቶች ለመከላከል የተደነገጉ ናቸው።" (205 ፣ 2007)

ሊብራል እንስታዊነት የሴቶችን አቅም በማንኛውም መንገድ ለማሳየት የሚጥር ንቅናቄ ሲሆን እያንዳንዱ ስራዎቹ የህግ ከለላ ያለው የሴቶችን እኩልነት ለማስከበር የተነሳ የእንስታዊንነት አይነት ነው። ኬቪን ሃሪሰን እና ቶኒ ቦይድ "ፌሚኒዝም" በሚለው መፅሃፋቸው ላይ እንዲህ ያብራሩታል። "ሊብራል እንስታዊነት ሙሉ በሙሉ ትኩረት አድርጎ የሚሰራው በድብቅ ህጋዊ እና ግልፅ ህጋዊ በሆነ መንገድ ህግ በማውጣት የሴቶችን መብት ማስከበር ላይ ነው።"[4] (303 ፣2018)

2.1.7.2. ራዲካል እንስታዊነት

ራዲካል እንስታዊነት ሴት ልጅ በምንም አይነት መንገድ ገደብ ሊኖርባት አይገባም ብሎ የሚያምን የእንስታዊነት አይነት ነው። ይህ ንቅናቄ ወግ ፣ ባህል ፣ እምነት የሚባለው ህግ ሴቶችን ለመጨቆንና ለማሰር የመጣ ነው ብሎ ያምናል። ሴት ልጅ በማህበረሰቡ ፣ በአስተዳደጓ ፣ በሃይማኖታ በመሳሰሉት አማካኝነት የፈለገችውን ነገር ከማድረግ እንዲህ አይነቱ ስርዓት ጫና ሊያደርግባት አይገባም የሚል ሃሳብ ይዟል። ተክሉ አስካሉ "የአመፃ መንገድ " በሚለው መፅሃፉ ላይ "ራዲካል ፌሚኒዝም ወንድ እና ሴት እኩል ናቸው! በሁለቱ ፆታ መሃል ያለው ልዩነት የጥምረት ሳይሆን የከረረ ቅራኔ ማሳያ ነው። አባዊ (አባወራነት) ስርዐት መደቆስ አለበት በሚሉ መርሆች የሚመራ በመሆኑ ለወግ ጠባቂዎች በአያሌው ፈታኝ እንደሚሆን ከምስረታቸው ጀምሮ የተገለፀላቸው ጉዳይ ነበር።" (206 ፣ 2007)

ራዲካል እንስታዊነት አሁን በሴቶች ላይ ያለውን እና ከዚህ በፊት የነበሩ ጭቆናዎችን ከዚህ ቡሃላ እንዳይኖሩ እንዲሁም ይህን አይነቱን አስተሳሰብ ጨርሶ ለማጥፋት የሚታገል የእንስታዊነት አይነት ነው። ለዚህም ምሳሌ በሃገራችን ኢትዮጲያ ሴት ልጅ ወጥታ ሰራ ከመስራት ይልቅ የሁልጊዜ እጣ ፈንታዋ የቤት እመቤት መሆን ነው። ይህ ልማድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው እንጂ የሴት ልጅ አፈጣጠር ለዛ ብቻ ሆኖ አይደለም። በመሆኑም ይሄ ንቅናቄ ይህን አስተሳሰብ እስከመጨረሻው ለማጥፋት የተነሳ ንቅናቄ ነው። ኬቪን ሃሪሰን እና ቶኒ ቦይድ "ፌሚኒዝም" በሚለው መፅሃፉ ላይ "ራዲካል እንስታዊነት የሴቶች ጭቆና ከበፊት ጀምሮ እስካሁን ሁሉም ማህበረሰብ ዉስጥ ያለ እንደሆነ እና ይህን አስተሳሰብ በቁጥጥር ማዋል የሚፈልግ ነው።"[5] (305 ፣ 2018) ይህም ማለት የሴት ልጅ ጭቆናን አስቀርቶ ወጥታ እንድትገባ እና ነፃነት እንዲኖራት ለማድረግ የሚሰራ እንቅስቃሴ ነው።

2.1.7.3. ጀንደር እንስታዊነት

ይህ ንቅናቄ ፆታ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን ነገር ግን ከተፈጥሮ በተገኘ ሳይሆን በፍላጎት ፆታን መሰየም ይቻላል ብሎ የሚያምን አስተሳሰብ ነው። እንዲሁም እንዲህ አይነቱ ስርዓት ምንም አይነት የማህበረሰብ

ጫና እንዳይኖርበት የሚል የህግ ፍቃድም ያለው ንቅናቄ ነው። አንድ ሰው ማንኛውም አይነት ፆታ ይዞ ቢወለድም የራሱን ፆታ ራሱ/ሷ መርጦ መሰየም የሚችልበት ንቅናቄ ነው። ተክሉ አስካሉ "የአመፃ መንገድ" በሚለው መፅሃፉ ላይ ጀንደር እንስታዊነትን "ጀንደር" የሚለው ቃል ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ማህበረሰባዊ አሊያም ልማደ ህይወታዊ ሁናቴን የሚወክል በመሆኑ አንድ ሰው ካደገ በኋላ እንደፍቃዱ/ዷ ወንድ አልያም ሴት ወይም ተሰይሞ ያልታወቀ መሆን ይችላል የሚል ፍቺ ይሏል።" (2007 ፣ 218)

በመሆኑም በጀንደር እንስታዊነት እሳቤ ፆታ ተፈጥሮአዊ ሳይሆን ፆታ በፍላጎት የሚገኝበት ስያሜ ነው። ይህም ማለት አንዲት ሴት አስተዳደጓ በወንዶች መሃል ከሆነ ወይም ደግሞ ውሎዋ ከወድንዶች ጋር ከሆነ የወንዶችን ባህሪ ፣ አረማመድ ፣ አለባበስ ፣ አነጋገር . . . እየተላበሰች ትመጣለች ይህ ማለት ደግሞ ድርጊቷ ሁሉ የወንዶች ይሆንና የወንድ ስያሜ ወደማግኘት ትሄዳለች ማለት ነው። በዚህ ላይም ጌኒ ኤፓስኩይ እና ብሬንተን ዊመር "ፌሚኒስት ፐርስፔክቲቭ" በሚለው መፅሃፋቸው ላይ ጀንደር እንስታዊነትን እንደዚህ ይበይኑታል። "ይህ አስተሳሰብ ማፅከል ያደረገው አንድ ሰው ሴት ሆኖ አልተወለደም ቢወለድም ተፈጥሮአዊ አቋማቸው ሳይገድባቸው ኢኮኖሚያዊ ፣ የግል እና ማህበራዊ ምርጫቸውን ማስተካከል ይችላሉ።"[6] (2011 ፣24) ይህም ማለት አንድ ሰው የትኛውንም ፆታ ይዞ ይወለድ ፆታውን የሚወስነው በአስተዳደጉ ውስጥ ያለው ሂደት ነው የሚል ትርጓሜን የሚሰጥ ነው።

2.1.8. የይዘታዊ ትንተና ምንነት

ይዘት ማለት ውጪውን አይቶ መፈየድ የማይቻል ውስጣዊ ፍቺ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ልብወለድ ርዕሱን አይተን በውስጡ የያዘውን ሃሳብ ሙሉ ልናውቅ አንችልም ምክኒያቱም ሃሳቡን ምናገኘው ገልጠን ሰናየው ነው። ይዘትም ልክ እንደዚሁ ሲገለጥ የሚገኘው ሃሳብ ነው ልንለው እንችላለን። ለተለያዩ ሰራዎች ትንተና ለመስጠት ዋነኛው እና አስፈላጊው ነገር ይዘት ነው። ምክኒያቱም ምንተነትነው ጉዳይ ሙሉ እና የተሳካ እንዲሆን የሚያደርገው ውስጣዊ ፍቺው ሲገኝ ነው።

የይዘትን ትርጉም በኪነ-ጥበብ ውስጥ ስንመለከት ይዘታዊ ተንተና ማለት በአንድ ልብ ወለድ ፣ ግጥም ፣ ተውኔት ፣ ፊልም ፣ ቴአትር . . .ወ.ዘ.ተ ላይ ለሚነሱ ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች የኪነ ጥበቦቹ ቅርፆች ከተገነቡበት ፍሬ ነገሮች አኳያ ትንተና የሚሰጥ ማለት ነው። እንዲሁም ድፍን የሆኑ ሃሳቦችን ሸንሽኖ መመልከት ወይም ሂስ መስጠት ማለትንም ያጠቃልላል። ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ አራት ምሁራኖች በጋራ የፃፉት የ"ኮንቴንት አናላይቲክ" መፅሃፋቸው ላይ ይዘትን እንደሚከተለው ያብራሩታል። " በማንኛውም ትምህርታዊ ሂደት ላይ ይዘት ከሌለ እርስበርስ መግባባት እና የአእምሮ መስፋት ሊኖር አይችልም። ምክኒያቱም እይታ የሌለው ሃሳብ ግልፅ መሆን ስለማይችል እና ድፍን ስለሚሆን ነው።"[7] (ቪቶሚር ኮቫኖቪክ ፣ ስሬኮ ጆክሲሞቪክ ፣ ድራጋን ጋሴቪክ ፣ ማሬክ ሃታላ 2017 ፣ 78) ስለዚህ ይዘት ለትምህርታዊ ክንውኖች እንደ ምሰሶ የሚያገለግል ነው። ይህም ማለት ማንኛውም ነገር በውስጡ የሚይዘው ነገር ከሌለ ባዶ ወይም ትርጉም የለሽ ነው ሚሆነው።

2.1.9. የተዛማጅ ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት

አጥኚዋ በ“ቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እና የረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና” በሚል ርዕስ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ በቀጥታ አላገኘችም። ነገር ግን በተዘዋዋሪ በቅድስት ይልማ “ታዛ” በሚለው ፊልም ላይ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍን እንደ ተዛማጅ ፅሁፍ በመጠቀም በሁለቱ ጥናቶች መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት እንደሚከተለው አስቀምጣለች። ይህም ጥናታዊ ፅሁፍ ዳግማዊ ተክሉ ስኔ 2010 ዓ.ም “ታዛ ፊልም ከማርክሲዝም እሳቤ አንፃር” በሚል ርዕስ ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ኦፍ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ሲሆን ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች የተከፋፈለ ነው። በምዕራፍ አንድ ላይ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት የጥናቱ መጠነ ርዕይ ፣ የጥናቱ አወቃቀር ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ የጥናቱ ጥያቄዎች እና በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች የሚሉትን የያዘ ሲሆን በምዕራፍ ሁለት ስለፊልም እና ስለማርክሲዝም ፅንሰ ሃሳብ ትንተና ይሰጣል። በምዕራፍ ሶስት ታዛ ፊልምን ከማርክሲዝም ፅንሰ ሃሳብ አንፃር ይተነትናል። በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳብ ሰጥቶ ያጠቃልላል።

የዳግማዊ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች በቅድስት ይልማ የተሰሩ ፊልሞችን ስለሚዳስሱ እና ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች ሰለ ፊልም ሰለሚያብራሩ ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ የዳግማዊ ተክሉ ጥናት “ታዛ ፊልምን ከማርክሲዝም እሳቤ አንፃር” በሚል የተሰራ ሲሆን ይሄኛው ጥናት ደግሞ ረቡኒ እና ሰላም ነው? የተሰኙ ፊልሞቿን ከግብዐተ ድምፅ ፣ ከፊልም ትወና እና ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር መተንተኑ ነው።

ምዕራፍ ሶስት

3. የመረጃ ትንተና

3.1. የቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ

ቅድስት ይልማ በሃገራችን ከሚገኙ እንስት ደራሲና አዘጋጆች መካከል አንዷ ናት። ቅድስት ይልማ ተወልዳ ያደገችው ባሌ ጎባ በምትባል ከተማ ውስጥ ነው። ነገር ግን ቅድስት እዚህ ነው የተወለድኩት ከማለት ይልቅ የተወለደችው በኢትዮጲያ በምትገኝ አንድ ሰፈር ውስጥ እንደሆነ በአንደበቷ ትናገራለች ። ቅድስት ከልጅነቷ ጀምሮ መሆን የምትፈልገው የፊልም ባለሙያ እንደነበር እንዲሁም ከ8ኛ ክፍል ጀምሮ ድርሰቶችን መፃፍ እንደጀመረች ራሷ ትናገራለች። ይህንንም ሃሳቧን ለማሳካት አባቷ አንባቢ ሰለነበር ከሱ ስር ሆና አንብቦ የጨረሳቸውን መፅሃፍቶች እያነሳች ታነብ እንደነበር ወላጆቿም እንደሚያበረታቷት ትናገራለች። የልጅነት ህልሟም ተሳክቶ አሁን በፊልም ኢንዱስትሪ ውስጥ ከሚጠሩ ሴት ደራሲና አዘጋጆች መካከል አንዷ ሆናለች። ቅድስት ይልማ "በጣም ብዙ መስራት አስባለው ያሰብኩትን ምንም ያህል ፐርሰንት ግን አልሰራሁም ብየ አስባለው" ትላለች። ከንግግሯ እንደምንረዳው ቅድስት ያለፈችባቸው ሁኔታዎች ሁሉ አሁን ላለችበት ደረጃ መሰረቶች እንዲሆኗት እንጂ እንዲነገርላት የምትፈልግ ሴት እንዳልሆነች መረዳት ይቻላል። ቅድስት በጣም በዙ ነገር መስራት የምትፈልግ እና ስራዎቿ ሁለት ነገሮች ላይ እንዲያተኩሩ ምትፈልግ እንስት ናት። ብዙ ጊዜም ምታነሳቸው ርዕሰ ጉዳዮች ሃገራዊ የሆኑ እና ያመነችባቸውን ነገሮች ነው። ይህም የሆነው እሷ ያመነችበት ከሆነ ምላሹ ጥሩ እንደሚሆን ሰለምታምን ነው። ሀገራዊ ጉዳዮችን ምታነሳው ደግሞ በሷ ፊልም አማካኝነት ለውጥ እንዲመጣ ሰለምትፈልግ ነው። ቅድስት ይልማ ከኪነ ጥበብ ስራዎች ዉስጥ እስካሁን ፊልም ላይ ብቻ ነው የሰራችው። እነዚህም በሃገራችን ያሉንን የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶች ያስተዋወቀችበት "ረቡኒ" ፣ እንዲሁም የወታደርን ስብዕና በተለያዩ መንገዶች ለማሳየት የሞከረችበት "ታዛ" ፣ ሴትነትን በማህበረሰባችን ከተለመደው የመደብ ስያሜ ለየት አድርጋ የሳለችበት ሰላም ነው? እንዲሁም በአርትስ ቲቪ ላይ የሚተላለፉ የትዕይንተ መፅሃፍት አጫጭር ፊልሞች በዝግጅት ሰርታለች። ከእነዚህም መካከል በአንዲት ሴት ላይ የሚያጠነጥን በአለማየሁ አብርሃም የተፃፈው "አልሀምዱሊላህ ደህና ናት" የተሰኘ መፅሃፍ ወደ ፊልም ቀይራ ያዘጋጀችው ተጠቃሽ ነው። ቅድስት እዚህ ሙያ ውስጥ ለመግባት ብዙ ፈተናዎችን እንዳሳለፈች ጓደኞቿም እሷም ይናገራሉ።

ቅድስት ይልማ "አንድ ሰው ፊልም ከመፃፉ እና ከማዘጋጀቱ በፊት የሚለው ነገር የሚያስተላልፈው መልዕክት ሊኖረው ይገባል" ትላለች። ቅድስት ፊልሞቿን ስትሰራ የምትጠቀማቸውን ቴክኒኮች ሌሎችም የፊልም ባለሙያዎች ቢጠቀሙት የተዋጣለት ፊልም እና የፊልም ኢንዱስትሪ መስፋፋት ይገኛል። ጓደኞቿ እንደሚናገሩት ቅድስት ይልማ በጣም የዋህ ፣ ለሰው አዛኝ ፣ ለቤተሰቦቿ ህይወቷን የምትሰጥ እንዲሁ በስራዋ ድርድር የማታውቅ ሁሉም ነገር ከስራ በኋላ ነው ሚመጣው ብላ የምታስብ በፊልም ኢንዱስትሪው ላይ ብቻ ትኩረቷን አድርጋ የምትሰራ የፊልም አዘጋጅ እና ደራሲ ነች። ቅድስት ከአንድ ሴት ልጇ ጋር እና ከቤተሰቦቿ

ጋር የምትኖር ሲሆን በአሁኑ ሰአት እረኛዬ የተሰኘ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ እና ሌላ ፊልም ጎን ለጎን እየሰራች ትገኛለች።

3.2 የረቡኒ ፊልም ታሪክ

አሪቲ በምትባል የገጠር ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ዮቶር የተባሉ ሰፊ የእፅዋት ማሳ ያላቸው የባህላዊ መድሃኒት ቀማሚ ነበሩ። ሃኪም ዮቶር የሚያሳድጓቸው ሁለት የልጅ ልጆች አሏቸው እነዚህም አደይ እና አቡሌ ይባላሉ። አደይ እና አቡሌ ወላጆቻቸውን ያጡት በልጅነታው ነበር በጊዜው አቡሌ በጣም ልጅ ሰለነበር እናቱ ሰትሞት አደይን እንደ እናቱ እያሰበ ሁሌም ቀሚሷን ይዞ ነበር በመንገድ ላይ ሚሄደው። ከእለታት በአንዱ ቀን አንድ ልዑል የተባለ ባለሃብት መሬት ለመግዛት ያስብና እና በደላላ አማካኝነት ወደ ሃኪም ዮቶር ማሳ መጥቶ ያናግራቸዋል። እኚህም ሰው ሃላፊነቱን ለልጃቸው አደይ እንደሰጡ ነግረውት እሷን እንዲያናግራት ያደርጋሉ። አደይም የተማረች እና ሰለመሬቱ ብዙ እውቀት ያላት ሰለሆነች መሬቱ ለሌላ ነገር መዋሉ ሰላላሳመናት የባለሃብቱን ሃሳብ ለማስቀየር ሁልጊዜ ለነገ ለነገ እያለች ቀጠሮ ታሲይዘዋለች። እናም በሚመላለስበት ጊዜ ሁሉ ማሳው ሰለሚያበቅለው ቅጠሎች እና ሰለመድሃኒትነታቸው ትነግረዋለች። ነገር ግን የእሱ ሃሳብ መሬቱ ላይ ኢንቨስት ማድረግ ሰለነበር የእሷን ንግግር ካንገት በላይ ነበር ሚሰማው። አደይም በጣም ብልህ ሰለነበረች በሆነ አጋጣሚ ወደ ውጪ ሃገር ሊሄድ እንደሆነ ሲነግራት "ሞሪንጋ" የተባለ መድሃኒት እንዲያመጣላት ትነግረዋለች። ከ3 ቀናት በኋላ ሲመለስ ያዘዘችውን መድሃኒት ይሰጣታል እሷም መድሃኒቱን ዞር ዞር አድርጋ አይታ ትወረውረዋለች። እሱም ደንግጦ ውድ ዋጋ እንደተገዛ ይነግራታል። እሷም ማሳቸው ዉስጥ ካለው አንድ ቅጠል አምጥታ ያመጣው መድሃኒት ከዚህ ቅጠል እንደተሰራ ትነግረዋለች። እሱም በዚህ ድንቅ አስተሳሰቧ ተረትቶ የመሬት መግዛቱን ሃሳብ ቀይሮ ሁሌም ወደማሳው እየሄደ ከሷ ጋር መዋል ይጀምራል። በዚህም ምክኒያት ከአደይ ጋር በጣም ይላመዱና ወደ ፍቅር ይገባሉ። ልዑል ግን ባለትዳር ሰለነበር ከአደይ ጋር ያለው ግንኙነት ትዳሩን ወዳልተፈለገ ጥላቻ ውስጥ ከቶት ከሚስቱ ጋር መጣላት ይጀምራል። ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት ልዑል አደይ እግር ላይ ተኝቶ እያወሩ ሚስቱ ትመጣባቸዋለች። ይህንንም ሄዳ ለአደይ ቤተሰቦች ትናገራለች። ቤተሰቦቿም እንዲህ አይነቱን ተግባር ከአደይ ስለማይጠብቁት በሷ ላይ የተለየ ቅያሜ ያድርባቸዋል። አደይም ባደረገችው ነገር ተፀፅታ ሁሉንም ይቅርታ ትጠይቃለች ልዑልም ሚስቱን ይቅርታ እንዲጠይቃት እና ወደነበረ ፍቅራቸው እንዲመለሱ ታደርጋለች። ከዚህም በኋላ ልዑል እና ሚስቱ ያለባቸውን የመውለድ ችግር የሚያክም መድሃኒት ትሰጣቸዋለች። ነገር ግን አደይ ከልዑል ፍቅር ይዟት ሰለነበር ከዚያ በኋላም ልታገኘው ትፈልጋለች። ነገር ግን ማንም የማያውቀው አያቶቿ ብቻ የሚያውቁት የነበረባት ህመም በድንገት ብሶባት ወደ ፀበል ለመሄድ ትወስናለች። ከመሄዷ በፊትም ልዑልን አግኝታ ራሷ እንደታመመች ሳይሆን እናቷ ስለታመመች ፀበል ሊሄዱ እንደሆነ እና ከሰባት ቀን በኋላ እንደሚመለሱ ነግራው ደብዳቤ ሰጥታው ይለያያሉ። ከሰባት ቀናት በኋላም ልዑል እንደለመደው ሊያገኛት ወደሷ ቤት ሲሄድ አደይ ሞታለች በዚህም ውስጡ ይሰበራል በመጨረሻም የልዑል ሚስት የሆነችው ርብቃ አደይ በሰጠቻቸው መድሃኒት አማካኝነት ታረግዛለች። ልዑል እና ርብቃም በሰላም መኖር ይጀምራሉ።

3.2.1. የረቡኒ ፊልም ርዕሰ ጉዳይ እና የቅድስት ይልማ የህይወት ተሞክሮ

3.2.1.1. የረቡኒ ፊልም ርዕሰ ጉዳይ

ረቡኒ መነሻ ሃሳቡ በሃገራችን መሬት የሚበቅሉ ነገር ግን የማንጠቀምባቸው በርካታ መድሃኒቶች እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች እንዳሉን ለማሳወቅ እንዲሁም እንደዚህ አይነት መሬትን አጥፍቶ ለሌላ ማንኛውም ነገር ማዋል ከማህበረሰቡ አልፎ ሃገርን እንደሚጎዳ የሚያሳይ ፊልም ነው። በዉጪ ሃገራት የሚገኙ የተለያዩ በውድ ዋጋ የሚሸጡ መድሃኒቶች እና ፀረ ተዋሲያን በኛው ሃገር የሚበቅሉባቸው ቦታዎች አሉ የሚል ጭብጥ የያዘ ነው። ይሄንንም በፊልሙ 23ኛው ትዕይንት ላይ 30፡55፡00 ደቂቃ ልዑል ለአደይ ሳኒታይዘር ሲሰጣት እሷም ከማሳቸው ውስጥ እንዶድ የተባለ 100% ጀርምን የሚገል ቅጠል አምጥታ ስትሰጠው ያሳያል። ይህም የሚያመለክተው የተለያዩ የባህል መድሃኒቶች እና ፀረ ተዋሲያን በሃገራችን ኖረው ነገር ግን እንዳልተጠቀምንባቸው ነው። በተጨማሪም 50ኛው ትዕይንት ላይ 51፡34፡00 ደቂቃ ልዑል ሞሪንጋ የተባለ መድሃኒት ከውጪ ሃገር አምጥቶ ሲሰጣት ይታያል ይህንንም መድሃኒት ወርውራ በድጋሚ ከማሳቸው ውስጥ ሽፈራው የተባለ ቅጠል አምጥታ ከኛው ሃገር ወስደው ለኛው እንደሚሸጡልን ስትነግረው ይታያል። ይህም የሚያሳየን ምድራችን ላይ ሚበቅል ሃብት በውጪ ሃገራት ተቀነባብሮ ሲመጣ ብዙ ገንዘብ እያወጡ መግዛቱ በሃገራችን ያለውን ሃብት ማራከስ እንደሆነ እና ተጠንቅቀን እንድጠቀመው ያስገነዝባል። እናም ይሄ ፊልም በሃገራችን ካሉ ብዙ እሴቶች መካከል የተወሰኑትን እንደ ምሳሌ አንስቷል ሰለዚህም የሃገራችንን ሃብት በአግባቡ እንጠቀምበት የሚል መልዕክት ያዘለ ነው። እንዲሁም አደይ የነበረባት የካንሰር ህመም እስከመቼ በህይወት ሊያቆያት እንደሚችል ሃኪም ዮቶር ሲናገሩ ይታያል። ይህ ደግሞ እኚህ ሰው በህይወታቸው ሲሰሩ የኖሩት የባህል ህክምና ይሄን እንዲያውቁ እንዳደረጋቸው ለማሳየት ችሏል። ለማሳያ በመጀመሪያው ትዕይንት ላይ 00፡02፡08 ደቂቃ ስንመለከት ያሳደጓት ልጃቸው አደይ በህይወት መቆየት የምትችለው ለስልሳ ቀናት ብቻ እንደሆነ ሲናገሩ ማየት ይቻላል።

3.2.1.2. የረቡኒ ፊልም ርዕሰ ጉዳይ እና የቅድስት ይልማ የህይወት ተሞክሮ

ፊልም ምንጊዜም ቢሆን በገሃዱ አለም የሚታዩ እና የሚሰሙ በህይወት ሂደት ዉስጥ ያሉትን የኑሮ ሂደቶች የሚንፀባርቅበት ነው። ደራሲው ወይም አዘጋጁ ባለው እውነታ ላይ ተመርኩዞ ውበት ፣ ድርጊት ፣ አስቂኝ ዘውግ እንዲሁም የተለያዩ ለተመልካች ስሜት እንዲቀርብ የሚያደርገውን መሰረታዊ ነገሮች በመጠቀም ሊፅፍ ወይም ሊያዘጋጅ ይችላል። ስለዚህ አንድ ደራሲ ወይም አዘጋጅ አንድ ፅሁፍ ሲፅፍ በአስተዳደጉ ፣ በአካባቢው ባሉ ተግባራት ፣ በንግርት ከሰማቸው ታሪኮች ፣ በሃገሩ ላይ ካሉ እሴቶች የራሱ የሆነ ምልከታዎች ይኖሩታል ማለት ነው።

ቅድስት ይልማ በረቡኒ ፊልም ላይ ለማሳየት የሞከረችው ከተወለደችበት እና ካደገችበት ከተማ አኗኗር እንዲሁም በራሷ ላይ በደረሰ አጋጣሚ በመነሳት ያሉንን ሃብቶች ለማሳየት ነው። ቅድስት ይልማ “በነገራችን ላይ . . .” በሚለው ደረጀ ሃይሌ በሚያዘጋጀው የቴለቪዥን ፕሮግራም ላይ ባደረገችው ቃለ መጠይቅ በድሮ ጊዜ አያቷ ሰፊ መሬት እንዳላቸው እና ይህንንም መሬት ባአካባቢያቸው ላሉ ማህበረሰቦች እንዲጠቅም አደርገው በመሬቱ

ላይ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን እያበቀሉ እንደሚሰሩበት ትናገራለች። የቅርብ ወዳጆቿም የረቡኒ ፊልም መነሻ የሆናት በእግሯ ላይ ቁስል ወጥቶባት በባህል ህክምና ስለዳነች ነው ይላሉ። የእነዚህን ሃሳቦች ቅንጅትም በዚህ ፊልም አማካኝነት አጋርታለች ማለት ነው። በዚህም ምክኒያት የረቡኒ ፊልም ከቅድስት ይልማ ተሞክሮ ጋር በትክክል እንደሚዛመድ ያሳያል።

3.2.2. የረቡኒ ፊልም ትወና

በረቡኒ ፊልም ላይ የተለያዩ ገፀ ባህሪያትን የተላበሱ ከ17 በላይ ተዋናዮች አሉ ከእነዚህም መካከል ሩታ መንግስተአብ ፣ አማኑኤል ሃብታሙ ፣ የአብስራ ተክሉ እና አብነት አየለ . . . ዋና ገፀባህሪያት ሚባሉትን የያዙ ናቸው። አጥኚዋም እነዚህን ተዋናዮች ከካሜራ ጋር ባላቸው ግንኙነት ውስጥ ደካማ እና ጠንካራ ጎን እንደሚከተለው በዝርዝር ትተነትነዋለች።

3.2.2.1. የረቡኒ ፊልም ከአካላዊ ትወና አንፃር

የአካላዊ ትወናን የሚወስኑት የገፀ ባህሪያቱ አይነቶች ናቸው። ይህም ማለት ገፀ ባህሪው ያለበት የእድሜ ክልል ፣ የአኗኗር ሁኔታ ፣ የሰውነት ክብደት መጠን ይወስነዋል። በረቡኒ ፊልም ላይ አራት ዋና እና የተለያዩ አይነት ገፀ ባህሪያት አሉ ሽማግሌ ፣ ህፃን ፣ ወጣት ፣ ጎልማሳ . . . እነዚህም አደይ ፣ ልዑል ፣ ሃኪም ዮቶር እና አቡሌ ናቸው።

የአደይ ገፀ ባህሪ የተሳለችበት መንገድ አጠር ያለ ቁመት ያላት ፣ መልከመልካም ፣ የልጅ ሳቅ ያላት ፣ እንደ ልጅ የምትጫወት ፣ ቀልድ የምትወድ ፣ የ3ኛ አመት ሳኒቴሽን ተማሪ ፣ አስተሳሰቧ ብልህ እና አስተዋይ የሆነች ሴት ሆና ነው። ይህንንም ገፀ ባሪ የምትጫወተው ተዋናይቷ ሩታ ስትሆን ሩታ ከአደይ ጋር የሚያመሳስላት መልከመልካም መሆኗ ብቻ ነው። ቢሆንም በዚህ ፊልም ላይ ተመልካች የአደይን ልጅነት ፣ ቅብጠት እና ቅልጥፍና በትክክል አምኖ እንዲቀበል ካደረገችበት ትወና መካከል አንዱ 24ኛው ትዕይንት ላይ 00:34:35 ደቂቃ ልዑልን ስላስኮረፉ እሱን ለማሳቅ ዳንሱን ምታሳይበት መንገድ የገፀባህሪዋን ልጅነት እና የተዋናይቷን ቅልጥፍና ለማሳየት በቂ ነው። እንዲሁም ነገሮችን ለማስረዳት ሰውን ለማስደንገጥ ፣ ለማዝናናት ሮጣ ሰውን በማሯሯጥ ፣ በመደነስ ትተውናለች። በዚህም በትክክል ተመልካቹ ገፀ ባህሪዋን እንዲረዳት እና ወጣት መሆኗን እንዲያምን አድርጋለች። ስለዚህ ሩታ ገፀ ባህሪዋ በሚመጥናት ልክ አደይን ተጫውታለች ማለት ነው።

ልዑል ጎልማሳ በሚባል የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሲሆን ረዘም ያለ ቁመት ያለው ፣ መልከመልካም ፣ ከሰው በተለየ መልኩ ቆሻሻን ሚጠየፍ ፣ ቆፍጠን ያለ አቋም ያለው ፣ የተረጋጋ ፣ በክብሩ እና በገንዘብ የማይደራደር ፣ የተማረ የፋብሪካ ባለሃብት እና ስራ አስኪያጅ ሆኖ ነው። ይህን ገፀ ባህሪ የሚጫወተው አማኑኤል ነው። ልዑል ከአማኑኤል ጋር የሚያመሳስለው ቁመቱ ፣ መልከመልካም መሆኑ እና እርጋታው ሲሆን ይህ ተዋናይ ልዑልን በሚፈለግበት ልክ ተጫውቶታል ማለት ይቻላል። ለምሳሌ 12ኛው ትዕይንት 00:13:20 ላይ ስንመለከት ገፀ ባህሪው ለራሱ የሰጠውን ክብር ረስቶ ሲሮጥ ይታያል። ስለዚህ እንቅስቃሴውን ቁጥብ እና የተረጋጋ ያደረገው የገጸ ባህሪው ተረጋግቶ መሳል ነው እንጂ ተዋናዩ በማንኛውም ደረጃ ሰውነቱን እያንቀሳቀሰ መተወን ይችላል።

እንዲሁም የተሳለበት እድሜ እንቅስቃሴውን ሊገድበው እንደማይችል ለማሳየት ስለተፈለገ ነው። አማኑኤልም በዚህ ልዑል የተሳለበትን መንገድ በደንብ እንዲታይ አድርጎታል።

አቡሌ ልጅ የሚባል እድሜ ላይ ያለ ሲሆን አጠር ያለ ቁመት ያለው ፣ ቀልጣፋ ፣ የደስደስ ያለው ፣ ተንኮለኛ ፣ እልኸኛ ፣ ለሰው የሚያዝን ፣ ወደፊት እንደ አያቱ የባህል መድሃኒት ቀማሚ መሆን የሚፈልግ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ነው። 4ኛው ትዕይንት ላይ 00:06:38 ደቂቃ ከ4ተኛ ወደ 5ተኛ ክፍል የተሸጋገረበትን ውጤት ለአደይ ለማሳየት የሚሮጠው ሩጫ በትክክልም የህፃን ሩጫ መሆኑን ያሳያል። አቡሌን ወክሎ የሚጫወተው ተዋናይ ያብስራ ከአቡሌ ጋር የሚያመሳስላቸው ተቀራራቢ እድሜ ላይ መሆናቸው ሲሆን ይህም ለያብስራ ትወና የሰውነት እንቅስቃሴ ፣ አረማመድ እና ቅልጥፍና ቀላል እንዲሆን አድርጎለታል። በመሆኑም በትክክል የአቡሌን ገፀ ባህሪ አሳምኖ ተጫውቶታል።

ሃኪም ዮቶር የሽምግልና እድሜ ላይ ያሉ የተረጋጉ ፣ ሰውን በጥበብ ማዳን የሚያስደስታቸው ፣ ሃዘናቸውን ደስታቸውን በውስጣቸው የሚይዙ ፣ ብልሃተኛ ናቸው። ሃኪም ዮቶር እና አቶ አብነት የሚያመሳስላቸው ሁለቱም በሽምግልና የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ መሆናቸው ነው። ገፀ ባህሪው እንደሌሎቹ ገፀባህሪያት የሰውነት እንቅስቃሴያቸው የፈጥነ እና ቅልጥፍ ያለ እንዲሆን ሰለማይጠበቅ በትክክል የአቶ አብነት ትወና ለሃኪም ዮቶር ይመጥናል። ካሉበት የእድሜ ክልል አንፃር የሰውነት እንቅስቃሴያቸው የተገደበ ነው። በረቡኒ ፊልም 40ኛው ትዕይንት ላይ 00:48:36 ደቂቃ እሳቸው ያዘዙትን ትዕዛዝ ሰዎቹ ሳይቀበሉ ሲቀሩ በንዴት ሲራመዱ ይታያል። በዚህ ትዕይንት ላይ እኚህ ሰው የሰውነት ትወናቸው የፈጠነ እና የተቀላጠፈ ቢሆነ ተዋናዩ በተፈለገው ልክ ተመልካችን ማሳመን አይችልም። ተመልካቹም ገፀ ባህሪውን እንደ ሽማግሌነቱ ሊቀበለው አይችልም። ነገር ግን ባሉበት የእድሜ ልክ እርምጃቸውም የተገደበ ነው። በዚህም ትወና አቶ አብነት ተመልካቹን ማሳመን ችሏል።

3.2.2.2. የረቡኒ ፊልም ትወና ከድምፅ አንፃር

የፊልም ትወና እንደ መድረክ ትወና ከፍተኛ ድምፅ አያስፈልገውም ምክኒያቱም በፊልም ትወና ላይ አብዛኛው ታሪክ ሚገለፀው በድርጊት እና በስሜት ስለሆነ ነው። ይህ ማለት ግን የፊልም ትወና ድምፅ አያስፈልገውም ማለት አይደለም። በፊልም ትወና ላይ ስሜት ያለው ድምፅ አወጣጥ ያስፈልጋል። ይህም ማለት አንድ ተዋናይ እየተንሾካሾከ ፣ በሲቃ ፣ በንዴት ፣ በመገረም... ሲያወራ ለእያንዳንዱ ስሜት በተለያየ ድምፀት ነው ሚተውነው ማለት ነው።

በረቡኒ ፊልም ላይም የአደይን ገፀ ባህሪ ምትጫውተውን ሩታ የተለያዩ ስሜቶችን በሚገልፅ ድምፀት ስትተውን እንመለከታለን። ለምሳሌ በፊልሙ 26ኛ ትዕይንት ላይ 00:36:44 ደቂቃ አደይ የውሸት ድንጋጤ ጩኸት ስትጮህ ይታያል ይህም ልዑልን ለማሳመን ያደረገችው ሲሆን በሷ የድምፅ ትወና አማካኝነት ድንጋጤውም ተመልካቹ ጋር እንዲጋባ አድርጋለች። በተጨማሪም 48ኛ ትዕይንት ላይ 1:00:28 ደቂቃ አደይ በለቅሶ እና በድንጋጤ ስሜት ውስጥ ሆና የምታወጣው ድምፀት ያለችበትን የድንጋጤ እና የሃዘን ስሜት በትክክል ገልፆታል። ነገር ግን 12ኛው ትዕይንት ላይ 00:13:09 ደቂቃ ላይ እየፈጠነች ስታወራ ቃላቶችን ስትደራርብ

ይታያል ፊልሙ ይሄ ደግሞ እንደ አንድ የፊልም ባለሙያ ሲታይ ስህተት ነው። ምክኒያቱም ተመልካች ፊልሙን በሚያይበት ወቅት እያንዳንዱን ቃለተውኔት መስማት እና መረዳት ስላለበት ነው።

የልዑል ገፀ ባህሪይን አማኑኤል እንዴት እንደተወነው ስንመለከት ደግሞ ትዕይንት 48 ላይ ልዑል 1፡00፡20 ደቂቃ በባለቤቱ ርብቃ ተናዶ ስለነበር በብስጭት ሲናገር ይታያል። ይኸውም የድምፅ አወጣጥ ጩኸት የተቀላቀለበት ስለሆነ በትክክልም ያለበትን ዉስጡ ያለውን የምሬት የመሰልቸት እና የንዴት ስሜት ለተመልካቹ አጋብቷል። በተጨማሪም ትዕይንት 87 ላይ 1፡44፡10 ደቂቃ አደይን አፍቅሯት ስለነበር መሞቷን ላለማመን ። ለቅሶ የተቀላቀለበት ሳቅ ሲስቅ እንዲሁም ዝብርቅርቅ ባለ ስሜት ዉስጥ የሚያወጣው ድምፀት በትክክል ያለበትን የተዘበራረቀ ስሜት ተመልካቹ እንዲረዳ አድርጎታል።

ያብስራ የተወነው የአቡሌ ገፀ ባህሪ በዚህ ፊልም ላይ የሚያወጣው ድምፅ በትክክልም ልጅነቱን የሚወክል ነው። ለምሳሌ በ21ኛው ትዕይንት ላይ 00፡28፡21 ደቂቃ የተሰማውን ስሜት እንደ ትልቅ ሰው ቀስ ብሎ ከማስረዳት ይልቅ እያለቀሰ ሲገልፅ ይታያል በዚህም የተሰማውን ስሜት በልጅነት ድምፅ አወጣጡ አማካኝነት የገለፀበት መንገድ ተመልካች ገፀ ባህሪውን በደንብ እንዲረዳው አድርጓል ማለት ነው። በተጨማሪም 51ኛው ትዕይንት ላይ 1፡04፡07 ደቂቃ በእልህ ሲያወራ ምላሱ ሲኮለታተፍ በትክክልም የህፃን ልጅ ድምፀት ነው ሚያወጣው። ስለዚህ ያብስራ አቡሌን በትክክል ህፃን መሆኑን ከንግግሮቹ መረዳት እናም ተመልካች በዚህ ምክኒያት ህፃን መሆኑን አምኖ እንዲቀበል አድርጎታል።

አቶ አብነት የሃኪም ዮቶርን ገፀ ባህሪይ በድምፅ አተዋወን የሚጫውቱበት መንገድ በትክክልም ሽማግሌነታቸውን አምነን እንድንቀበል አድርግጎናል። ይህ የሆነበት ምክኒያትም አቶ አብነት ያሉበት እድሜ ለገፀ ባህሪው የቀረበ ስለሆነ የሚያወጡት ድምፅ እንዲያሳምን ሆኗል። ነገር ግን አንዳንድ ትዕይንቶች ላይ ቃለ ተውኔታቸው ስሜት አልባ ነው። ይህንንም ማሳያ 43ኛው ትዕይንት ላይ 00፡49፡50 ደቂቃ ስንመለከት ስሜቱ የተግሳፅ ነው ነገር ግን እሳቸው ቃለ ተውኔቱን ብቻ ቃል በቃል ብቻ ስለሚሉት ስሜት እንዳይሰጥ አድርጎታል።

3.2.2.3. የረቡኒ ፊልም ትወና ከስሜት አንፃር

በፊልም ላይ የመጀመሪያው እና አስፈላጊው ነገር ስሜት ነው ምክኒያቱም ካሜራው ከተዋናዩ ጋር ያለው ቁርኝት የጠበቀ ሰለሆነ እያንዳንዱን ስሜት ለተመልካቹ ለማጋባት ተዋናዩ ጥሩ ስሜት ያለው አተዋወን ሊተውን ይገባዋል። ይህም ማለት ከንግግር ይልቅ በስሜት ሚገለፁ ለምሳሌ ፀፀት ፣ መደነቅ ፣ ተንኮል ማሰብ ፣ ማዘን... የመሳሰሉት ስሜቶች ከንግግር ይልቅ በድርጊት እና በስሜት ቢገለፁ የበለጠ ተመልካቹጋ ስሜቱ እንዲጋባ ያደርጋርል። ስለዚህም በትወና ላይ ስሜት በጣም አስፈላጊ ጥበብ ነው። ስሜት በተለያዩ የሰውኔታችን ክፍሎች ሊገለፅ ይችላል እነዚህም በአይን ፣ በአፍ ፣ በአንገት ፣ በእጅ ናቸው ። በአይን የፍቅር ስሜት ፣ በአንገት የአጋንታ እና የአሉታ ስሜት ፣ በአፍ የማሽሚጠጥ ፣ የፈገግታ እና የማኩረፍ ስሜት ፣ በእጅ ደግሞ የመጠቆም ስሜቶችን ለመግለፅ እንጠቀምባቸዋለን። በረቡኒ ፊም ላይም እነዚህን ስሜቶች እና እነዚን ስሜቶች ለማሳየት የተጠቀሟቸውን የሰውነት ክፍሎች አክለን እንመለከታለን።

በመጀመሪያ ሩታ የምትጫወታትን የአደይን ገፀ ባህሪ ስንመለከት በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ስሜቷ ሲለዋወጥ ይታያል ለምሳሌ 48ኛው ትዕይንት ላይ 1፡00፡15 ደቂቃ ስሜቷ ከሳቅ ወደ ለቅሶ ሲለወጥ ፊቷን በማጨማደድ ፤ አይኗን በማጥበብ ፊቷ ላይ በደንብ ገልፃዋለች። ይህም ተመልካቹ የፊቷን ገለፃ ተከትሎ የገፀባህሪዋን ስሜት እንዲጋራ አድርጎታል። በተጨማሪም 83ኛው ትዕይንት ላይ 1፡33፡51 ደቂቃ አንገቷን በማዞር ያለችበትን የተስፋ መቁረጥ ስሜት በፊት ገለፃዋ ደግሞ ጭንቀቷን ስትገልፅ ይታያል። ይህም ሩታ ምን ያህል የገፀባሪዋን ስሜት ተረድታ ለተመልካች እንዲጋባች ያየንበት ስሜት ገላጭ ትወና ነው።

አማኑኤል የወከለውን የልዑል ገፀ ባህሪን ስንመለከት ደግሞ ትዕይንት 10 ላይ 00፡9፡46 ደቂቃ ለክብሬ አይመጥንም ብሎ ያሰበውን ነገር ሲሰማ የስላቅ ሳቅ ሲስቅ ይታያል። ይህም በአፍ አማካኝነት ከሚገለፁ ስሜቶች መሃከል አንዱ ነው ማለት እንችላለን። እንዲሁም 87ኛው ትዕይንት ላይ 1፡44፡20 ጀምሮ የአደይን መሞት ላለማመን የሚያሳየው የስላቅ ፊት ስሜቱን ገልፆለታል። በመሆኑም አማኑኤል በዚህ ትወናው የልዑልን ገፀባህሪ አምነን እንድንቀበል እና እንድንረዳው አድርጓል።

ያብስራ እድሜውም ልጅ ሰለሆነ የአቡሌን ገፀባህሪ ስሜቶች በትክክል ተጫውቷቸዋል። አቡሌ ያለበትን የልጅነት እድሜ ሳይሆን በውስጡ ያለውን ትልቅ ተስፋ እና ምኞት ፊቱን እንደ ጀኛ ኮስተር በማድረግ እና እጁን ጨብጦ ደረቱን በመምታት 81ኛው ትዕይንት 1፡27፡04 ደቂቃ ላይ ስሜቱን ሲያንፀባርቅ እንመለከታለን። በዚህም የአብስራ የስሜት ትወና አቅም አቡሌን በደንብ እንድንረዳው አድርጎናል። እንዲሁም በ87ኛው ትዕይንት ላይ 1፡46፡41 ደቂቃ ላይ አደይ ሰለሞተች በእጁ የሚይዘው ነገር አጥቶ እጆቹን እግሮቹ መካከል ከትቶ ተሸማቆ ድምፅ ሳያሰማ ሲያለቅስ ይታያል። ይህም በትክክል የደረሰበትን ጉዳት በትክክል የሚያሳይ ትወና ነው። በዚህም ያብስራ አቡሌ ምን አይነት ስሜት እንዳለው በግልፅ እንድናውቅ አድርጎናል።

አቶ አብነት የሃኪም ዮቶርን ስሜት በትክክል አንፀባርቀዋል ማለት ይቻላል። ይህም የሆነው በመጀመሪያ የአቶ አብነት እና የሃኪም ዮቶር እድሜ ተቀራራቢ በመሆኑ ነው። ሌላው ደግሞ የሚጠቀሙት የፊት ገለፃ በትክክል ያሉበትን እድሜ የሚገልፅ ነው። ለምሳሌ ትዕይንት 78 ላይ 1፡22፡18 ደቂቃ ትንፋሻቸው እየተቆራረጠ ተንፍሰው በአደይ ተስፋ ቆርጠው ሲሄዱ ፊታቸው ላይ ያለው ስሜት እጅግ ግራ የተጋባ እና የንዴት ፣ የማዘን እንደሆነ በደንብ ይታያል። እነዚህንም ስሜቶች አንገታቸውን በማዞር እና ፊታቸውን በማደብዘዝ ይገልጿቸዋል። ይህም አቶ አብነት የሃኪም ዮቶርን ስሜት አጋብተውብናል ለማለት ያስችለናል።

3.2.1. የረቡኒ ፊልም ግብዐተ ድምፅ አጠቃቀም

በረቡኒ ፊልም ላይ ፊልሙ የበለጠ ሳቢ እና ተወዳጅ እንዲሆን የተለያዩ ሙዚቃዎች እና ተፈጥሮአዊ ድምፆችን ተጠቅሟል። እነዚህንም አጥኚዋ ተፈጥሮአዊ ድምፅ እና የሙዚቃ ድምፆች ብላ እንደሚከተለው ታስቀምጠዋለች።

3.2.3.1 የረቡኒ ፊልም ተፈጥሮአዊ ግብዓተ ድምፅ

ይህ ፊልም የተለያዩ ቦታዎች ላይ የተፈጥሮ ድምፆችን በተገቢው ቦታ ይጠቀማል። ይህንንም ለማሳየት ትዕይንት 3 ላይ 00፡5፡51 ደቂቃ በጫካ ውስጥ ልጆች እየዘመሩ ሲሄዱ ጫካ ውስጥ እንዳሉ የሚገልፅ የአእዋፋት ድምፅ

ይሰማል ፣ ትዕይንት 4 ላይ 00፡6፡55 ደቂቃ የወንዝ ድምፅ ይገባል ይሄም በትክክል አደይ ያለችበትን ፏፏቴ ያለው ጫካ ቦታን ይግልፃል። ትዕይንት 8 ላይ 00፡14፡13 ደቂቃ በነአደይ ቤት በረንዳ ላይ አደይ ፣ ልዑል እና የልዑል የስራ ባልደረባ አማን ቁጭ ብለው ሲያወሩ ያሉበት ቦታ ድባብ እንዲኖረው አነስ ባለ ድምፅ እንደ ማጀቢያ የከብት ፣ የፍየል እና የዶሮ ድምፅ እንዲገባ ሆኗል። ይህም በዚሁ ደቂቃ ላይ አደይ ሁሉም የተሰማሩበትን የስራ አይነት ሰለምትዘረዝር በዛ ዉስጥ ከብቶች ዶሮዎች እንዲሁም የተለያዩ እንስሳቶች እንዳሉ ስለሚገልፅ ቃለ ተውኔቷም ለድምፆቹ መግባት ማሳመኛ ሆኖላታል። በአጠቃላአይ ፊልሙ የተሰራው በገጠራማው አካባቢ ሰለሆነ የከብቶች ድምፅ ፣ የዶሮዎች እንዲሁም የአእዋፋት ድምፅ መግባቱ ያሉበትን የገጠር ድባብ ለማምጣት አግዞታል። እነዚህ ድምፆች በመግባታቸው የፊልሙ መቼት የበለጠ ተአማኒነት እንዲኖረው አድርጎታል።

3.2.3.2. የረቡኒ ፊልም የሙዚቃ ግብዐተ ድምፅ

በረቡኒ ፊልም ላይ አብዛኛውን ቦታ የሚጠቀሙት የባህል ሙዚቃ መሳሪያ ነው። ይህም የሆነበት ምክኒያት በመጀመሪያ ፊልሙ አብዛኛውን ቦታ ሚያተኩረው በገጠር ውስጥ ስለሆነ ነው። ፊልሙ ሲጀምር የሚጠቀመው የበገና ድምፅ ሃኪም ዮቶር መድሃኒት ሲቀምሙ የተመስጥኦ ስራ በገና ብዙውን ጊዜ ለጥሞና ስለምንጠቀመው ድምፁ የሁኔታው እና የድርጊቱን ድባብ በማምጣት በትክክለኛው ቦታ ላይ ገብቷል።

በሌላኛው ትዕይንት ደግሞ ሁሉም በትካዜ እና በሃሳብየተዋጡበትን ስሜት በ ዋሽንት ሲደግፈው ይታያል። ዋሽንትም እንደሚታወቀው በሃገራችን ሰዎች የውስጣቸውን ስሜት ማለትም ሃዘን ፣ ደስታ ፣ ቁጭት ... የመሳሰሉትን ስሜቶች ወደሰው የሚያስተጋቡበት ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ነው። በመሆኑም በዚህ ፊልም ላይም በትክክለኛው ሰአት እና በትክክለኛው ቦታ ላይ ተጠቅሞ የጭንቀት እና የትካዜውን ድባብ ወደ ተመልካቹ አስተጋብቷል። ወደመጨረሻው 1፡45፡20 ላይም እንደዚሁ ያለውን የለቅሶ ድባብ ለማምጣት ዋሽንት ይጠቀማሉ በዚህም ድባቡ የሰው ስሜት ውስጥ ሰርፆ እንዲገባ አድርጎታል። በተጨማሪም ትዕይንት 28 ላይ 00፡39፡52 ደቂቃ በልዑል መኪና ውስጥ ባለው ቴፕ የተከፈተው ሙዚቃ ልዑል ከአደይ ፍቅር እየያዘው እንደሆነ ሚጠቁም ነው። ስለዚህ በዚህ ፊልም ላይ የገቡ እያንዳንዱ ሙዚቃዎች ምክኒያት አላቸው።

3.3. የሰላም ነው ፊልም ታሪክ

በጅማ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ሰላም ፣ ሞገስ እና ፍቅር የተባሉ ልጆች ነበሩ እነዚህ ልጆች እናታቸውን ያጡት በልጅነታቸው ነበር። በዚህም ምክኒያት ከናታቸው የወረሱትን የመጀመሪያዋ ሴት ልጅ እንጀራ በመጋገር ወንዱ በእንጨት ቅርፃቅርፅ በመስራት የመጨረሻዋ ሴት ልጅ ደሞ በስርቆት ራሳቸውን ያስተዳድሩ ነበር። ነገር ግን የፍቅር ስራ ሁልጊዜ ወንድምና እህቷን ያስከፋቸዋል ነገር ግን ልጅቷ ይህንን ስራ ማቆም አልቻለችም። በዚህ ሁኔታ እየኖሩ ሳለ ከ20 አመታት በኋላ ትቷቸው ሲኖር የነበረ አባታቸው በአክስታቸው አማካኝነት ሊያገኛቸው እንደሚፈልግ ይነግራቸዋል ነገር ግን የመጀመሪያዋ ሴት ልጅ እና ወንዱ ሊጅ በዚህ ሃሳብ አልተስማሙም ምክኒያቱም ያለፉበትን ችግር ሰለሚያስታውሱ። ነገር ግን ፍቅር የሚኖሩትን ኑሮ ሰለማትፈልገው እና ደግሞ

ወንድሟን ማሳከም ስለምትፈልግ የግድ አባቷን ቀርባ የአባቷን ሃብት መዝረፍ እንዳለባት አስባ ከእህትና ወንድሟ ተደብቃ አክስቷ ጋር ትሄዳለች። አክስቷም ከአባቷ ጋር ታገናኛታለች አባቷም የእውነት ፍቅሩን ሊያሳያት ቢሞክርም እሷ የመጣችበት አላማ የአባቷን ንብረት ወስዳ ወንድሟን ማሳከም ሰልለሆነ ሁልጊዜ ለአባቷ የምታሳየው ፊትም የማስመሰል ነበር። ይሀን አላማዋን ለማሳካትም የአባቷን ከቤት መውጣት ጠብቃ ከካዝና ውስጥ ገንዘብ ሰርቃ ልትሄድ ስትል በፖሊስ ቁጥጥር ስር ትውላለች በመጨረሻም የእስር ጊዜዋን ጨርሳ ወደቤት ስትመለስ አባትየው ወንድሟን አሳክሞት ሁሉም ነገር ተስተካክሎ ታገኘዋለች።

3.3.1 ሰላም ነው? ፊልም ከጀንደር እንስታዊነት አንፃር

በሰላም ነው? ፊልም ላይ ፍቅርን ያሳደጓት እህት እና ወንድሞቿ ናቸው። ፍቅር የሰፈር ጓደኞቿ በሙሉ ወንዶች እና ሌቦች ናቸው። ፍቅርም ከነሱ ጋር መዋል ባመጣባት ተፅዕኖ ምክኒያት አረማመዷ ፣ አነጋገሯ ፣ አለባበሷ ሁሉ እንደወንድ ሆነ። ስለዚህ በዚህ ፊልም ላይም ፍቅር የተሳለችበት መንገድ ወንድ በሚያስብላት ደረጃ ነው። ይህም ከሰው ጋር ስታወራ እንደ ወንድ ፀጉሯን እየጠቀለለች ፣ ስተራመድ እንደ ወንድ እየነጠረች ፣ አለባበሷ ሰፋፊ ሱሪዎች እና ኮፊያ ያላቸው ሹራቦች ቡትስ ጫማዎች ነው።

በሃገራችን ዉስጥ አሁን ባለንበት ደረጃ ደግሞ ለወንድ እና ለሴት ልጅ የተሰጠ የስራ ድርሻ እና መደብ አለ ማለትም አንዲት ሴት ኑሮዋን ለማስተካከል በቤቷ የማጀት ሰራዎችን ትሰራለች ፣ ቢሮ ተቀጥራ መስራት ትችላለች ከባሰ ደግሞ ሰው ቤት ተቀጥራ ልትሰራ ትችላለች። . . . ወንድ ደግሞ ቢሮ ሊሰራ ይችላል ፣ ከባድ ሰራዎች ሊሰራ ይችላል አለፈ ከተባለ ያለምንም ስራ ሰፈር ውስጥ መዋል ይጀምራል ተስፋ ሲቆርጥ ሌብነትን እንደ ስራ ይይዘዋል ። በኛ ሃገር የተለመደውም ሚታወቀውም ይሄ ነው። ፍቅር ግን እነዚህን ድርጊቶች የወንድ ብቻ ናቸው ብላ አልተወቻቸውም በፊልሙ ላይ እነዚህን ድርጊቶች ስትፈፅማቸው ይታያል። ፍቅርም በዚህ ፊልም ላይ በማህበረሰቡ ሚሰጣት የሴትነት ፆታ መደብ በምታደርገው ድርጊት አማካኝነት እንዲቀየር አድርጋዋለች። ነገር ግን ፍቅር ወደዚህ አይነት የወንድ ተግባር እንድትገባ ያደረጋት በሴትነቷ የሚደርስባትን ችግሮች ሁሉ ለመጋፈጥ እና የቤተሰቧን ህይወት ለመለወጥ እንጂ ሴትነት አንሶባት ወይም አስጠልቷት እንዳልሆነ በፊልሙ መጨረሻ ላይ ፍቅር ሲይዛት ሁሉንም ነገር ትታ ወደ ሴትነቷ ተመልሳ ኑሮዋን ስትቀጥል ይታያል። በኛ ሃገር ተቀባይነት አይኑረው እንጂ ጀንደር እንስታዊነት ይሄንን ሃሳብ እንደ ሴት ልጅ መብት አስቀምጦታል። አጥኚዋ ግን ይህን ሃሳብ ሴት ልጅ የፈለገችውን መስራት ትችላለች የሚለውን ነው እንጂ የፆታ ስያሜዋን ቀይራ እንደ ወንድ ትኑር የሚለውን ሃሳብ እምብዛም አትደግፈውም ምክኒያቱም የኖረችበት አኗኗር ፣ ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ ማህበረሰብ የሚባሉ አስተሳሰቦች ስላሉ በዚህ አስተሳሰብ ተምራ በማደጓ ይህንን አስተሳሰብ እንዳትደግፍ ተፅእኖ አሳደረባት እንጂ ከማህበረሰቡ ውጪ በሆነ መንገድ ስታየው ትክክል ነው ብላ ታምናለች።

ምዕራፍ አራት

4.1 ማጠቃለያ

የኢትዮጲያ ፊልም ኢንዱስትሪ አሃዱ ብሎ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስ የተለያዩ በፊልሙ ኢንዱስትሪ ውስጥ የራሳቸውን አሻራ የጣሉ ኢትዮጲያውያን የፊልም ባለሙያዎች አሉ። በዚህ ጥናትም በሃገራችን ኢትዮጵያ በኪነ-ጥበብ ኢንዱስትሪ ውስጥ በተለይም በፊልሙ ዘርፍ ላይ ጉልህ ሚና ካላቸው እንስቶች መካከል አንዷ ሰለሆነችው ደራሲ ፣ አዘጋጅ እና ፕሮዲዩሰር ቅድስት ይልማ የህይወት ታሪክ እንዲሁም ከፊልም ከሰራዎቿ መካከል ለረቡኒ እና ሰላም ነው? ፊልሞች ይዘታዊ ትንተና ተሰጥቷል።

በዚህ ጥናትም ቅድስት ይልማ የታውቀችበት ፊልም ረቡኒ በመሆኑ አጥኚዋ ረቡኒ ከቅድስት ይልማ የህይወት ተሞክሮ ጋር ያለውን ግንኙነት ፣ በረቡኒ ፊልም ላይ የፊልም ትወና ከአካላዊ ፣ ከድምፅ እና ከስሜት አንፃር እንዴት ተገልጿል ፣ የረቡኒ ፊልም የተፈጥሮአዊ እና የሙዚቃ ግብዐተ ድምፆች አጠቃቀም ምን ይመስላል የሚለውን ተንትናለች እንዲሁም ሰላም ነው? የተሰኘው ፊልሟን ከጀንደር እንስታዊነት ማለትም ሴት ልጅ በራሷ ፍቃድ እና ማህበረሰቡ በሚሰጣት የፆታ መደብ መኖር ትችላለች ከሚል ሃሳብ ጋር አዛምዳ ተንትናለች። በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ቅድስት ይልማ ከስራዎቿ ጋር ያላትን ግንኙነት ፤ መነሻ ሃሳቦቿን እና ወደፊት በኪነጥበቡ ዘርፍ ማሳረፍ የምትፈልገው አሻራ እንዳለ እንዲሁም ለፊልም ባለሙያዎች እንደመነሻ የሚያገለግሉ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።

ጥቅሶች በመግኛ ቋንቋቸው

1) The biography is indeed a genre one spanning a number of radically different typs of life story telling. Biography can be defined as genre, a narrative form and ana analytic field.

2) Biography is the study of the real individual. It is a generic term, covering the multitude of ways in Which we record individual human lives, past and present.

3) Feminist believe that there is a fundamental power struggle betweenmen and women. This, like the Struggles around class and Race, is potentiallyrevolutionary.

4) Libral feminism focus on the full extension of civil and legal rights to women by legislation.

5) Radical feminism holds that the suppression of women is a fundamental feature of almost all societies, past and present , and is the most profound of all the tyrannies.

6) central to this perspective is the concept that one is not born a woman. That women must transcend their natural position and choose economic, personal and social freedom.

7) without content there can not be edicuation since it is the process of intellectually interacting with the content that results in changes in learner's understanding , the learner's perspective , or cognitive structures of the learner's mind.

ዋቢ መጽሃፍት

ተክሉ አስካሉ። የአመፃ መንገድ። (2007)።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ (ፕሮፌሰር)። የምርምር መሰረታዊ መርሆች እና አተገባበር። ባህርዳር ዩኒቨርስቲ። (2009)።

አዲስ ተስፋዬ። የፊልም ድርሰት አፃፃፍ ብልሃት። አዲስ አበባ። ኩራዝ ማተሚያ ድርጅት። (2005)።

ወሰንየለህ ጥላሁን ገ/የሱስ። የፊልም ጥበብ ቅኝት። አዲስ አበባ። ፋር ኢስት ትሬዲንግ። (2005)።

ዳዊት ግርማ። እንስታዊነት በኢትዮጲያ ፍልስፍና ፤ ሃተታ ዘርአ ያዕቆብ እና ሃተታ ወልደ ህይወት እንደማሳያ። ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ። (2011)።

ጳውሎስ አዕምሮ። የፊልም አዘገጃጀት ዘይ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (2010)።

Birgitte Possing, Understanding Biographies, Universty press of southern Denmark, Specialtrykkeriet Viborg A/S, (2017).

Kevin Harrison & Tony Boyd, Feminism, Manchesteropenhive, (2018).

Nigel Hamilton and Hans Renders, The ABC of Modern Biography, Amsterdam Universty press B.V, (2018).

Penny A. pasque & Brenton wimmer, An Introduction Feminist Perspectives, VACPA College Student Education International.

Vitomir Kovanovic, Srecko Joksimovic, Dragan Gasevic, Marek Hatala (2017). Content Analaytic: The definition, scope, and an overview of published research. Society for learning Analytics Research.

ቃለ መጠይቅ

ቅድስት ይልማ። ስለ አዲሱ ፊልሟ። በደረጀ ሃይሌ። Benegerachin_lay_@Arts_Tv_world።

ሃምሌ 11/2013 **ዓ.ም።**

ቤተልሄም አለባቸው። ስለ ቅድስት ይልማ ስብዕና። በምኞት ወርቁ። በስልክ። ሃምሌ 6/2013 **ዓ.ም። ምሽት** 3፡08።

ቅድስት ይልማ። ስለ ፊልም ስራዎቿ። በምኞት ወርቁ። በስልክ። ወልቂጤ ፣ አዲስ አበባ።

ሃምሌ 9/2013**ዓ.ም። ጠዋት** 5፡25።

አባሪ